# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ትንተና

# (በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ተተኳሪነት)


በኀይሉ አባይ



2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ትንተና
# (በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርኀ ግብር

አማርኛን ለማስተማር ለኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት


በኀይሉ አባይ

አማካሪ፡- ሙሉሰው አስራቴ (ዶ/ር)



2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርኀ ግብር

### የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ትንተና

### (በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ተተኳሪነት)

አማካሪና ፈታኞች

| የአማካሪ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ሙሉሰው አስራቴ (ዶ/ር) | ________ | ________ |

| የፈታኞች ሥም | ፊርማ | |
|---|---|---|
| ________ | ________ | ________ |
| ________ | ________ | ________ |

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪፈጸም የጥናቴን ረቂቅ አንብበው ገንቢ አስተያየት በመስጠት፣ አቅጣጫ በማሳየትና በማቃናት ጥናቱ አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ሙሉሰው አስራቴ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የተመረጡትን መማሪያ መጻሕፍት እና ለጥናት የሚያግዙኝን የተለያዩ ጽሑፎች ያለምንም መሰልቸት በማንበብ ለተባበሩኝ የቀራኒዮ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ምስጋናናዬ ከልብ ነው፡፡ ከኢንተርኔት የሚያስፈልጉኝን ጽሑፎች በማውረድ፣ በትንተና ወቅት ሰንጠረዦችንና ለአስረጅነት ከመጻሕፍቱ ተቆርጠው የወጡ ጽሑፎችን በጥናቴ አስማምቶ በማቅረብ፣ በብሬል የጻፍኩትን ጽሑፍ ወደቀለም ጽሑፍ በመቀየርና አርትዖት በመስጠት ላገዘኝ ለመምህር አሻግሬ ግባቱ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት እድል በመስጠት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለምርምር ማካሄጃ የሚያስፈልጉኝን ወጭዎች በመሸፈን እንዲሁም የትምህርት ክፍሉ መምህራን ለህይወቴና ለስራዬ የሚጠቅሙ ትምህርቶችን በማስተማር ስላገዛችሁኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ....................................................................................i
አጠቃሎ ....................................................................................iv
ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ..................................................................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ..................................................................... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..................................................................... 2
1.3 የጥናቱ ዓላማ ..................................................................... 3
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ..................................................................... 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ..................................................................... 4
1.6 የጥናቱ ወሰን ..................................................................... 4
ምዕራፍ ሁለት፡-ክለሳ ድርሳናት ..................................................................... 5
2.1 የመጻፍ ክሂል ምንነት ..................................................................... 5
2.2 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ..................................................................... 6
2.3 የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች አደረጃጀት ..................................................................... 8
2.3.1 ተከታታይነት ..................................................................... 10
2.3.2 ተለጣጣቂነት ..................................................................... 13
2.3.3 ውህደት ..................................................................... 18
2.4 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..................................................................... 18
ምዕራፍ ሶስት፡-የጥናቱ ዘዴ ..................................................................... 22
3.1 የጥናቱ ንድፍ ..................................................................... 22
3.2 የመረጃ ምንጮች ..................................................................... 22
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ..................................................................... 23
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ..................................................................... 23
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና ..................................................................... 25
4.1 ከተከታታይነት አንጻር ..................................................................... 25
4.2 ከተለጣጣቂነት አንጻር ..................................................................... 32
4.2.1 ከቀላል ወደከባድ አደረጃጀት ..................................................................... 33

4.2.2 ከተጨባጭ ወደረቂቅ አደረጃጀት ........ 39
4.2.3 ከቅርብ ወደሩቅ አደረጃጀት ........ 40
4.2.4 ከቀድሞ መጥ አንጻር ........ 44
4.3 ከውህደት አንጻር ........ 48
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ ........ 50
5.1 ማጠቃለያ ........ 50
5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 52
ዋቢ ጽሑፎች ........ 54

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁበትን መንገድ መፈተሽ ነው። ለዚህም ጥናቱ አይነታዊ ምርምርን ተግባራዊ አድርጓል። አደረጃጀቱን በተከታታይነት ስር ተደጋግመው የመጡ ይዘቶች ያላቸውን የድግግሞሽ መጠንና የድግግሞሻቸውን ተገቢነት፣ በተለጣጣቂነት ስር ከቅርብ ወደሩቅ፣ ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅ እና ከቀድሞ መጥ አንጻር እንዴት እንደተደራጁና ከውህደት አንጻር ደግሞ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከሌሎች ትምህርቶች ጋር መደራጀት አለመደራጀቱ ተፈትሿል። የሰነድ ፍተሻ የተነሱትን ጉዳዮች ለማጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት አገልግሏል። በሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ በብዛት በአይነት በአይነት በመሰብሰቡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው የመረጃ መተንተኛ ስልት በአመዛኙ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ነው። ጥቂት የቁጥር መረጃዎች ስላሉ፣ ቀላል የድምርና የመቶኛ ስሌቶች በትንተናው ውስጥ ስላገለገሉ በተወሰነ ደረጃ መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትም በጥናቱ ውስጥ አገልግሏል። በመሆኑም አተናተኑ ቅይጥ ስልትን የተከተለ ነው። የጥናቱ ውጤትም የሚያሳየው በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተከታታይነታቸውና ተለጣጣቂነታቸው በተገቢውና ንድፈ ሀሳቡ ላይ በሰፈሩት መልኩ እንዳልቀረቡ ጥናቱ አሳይቷል። ተተኳሪ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተደጋግመው የቀረቡበት መጠን በቂ እንዳልሆነና ተማሪዎችንም የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ ብቁ እንዳልሆኑ በትንተናው ታይቷል። በተመሳሳይ ሁለቱም መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅና ከቀድሞ መጥ አንጻር ከመደራጀት አንጻር በከፊል ጠንካራ ጎን ያላቸው ሲሆን በከፊል ደግሞ ድክመት ታይቶባቸዋል። ከቅርብ ወደሩቅ ያላቸው አደረጃጀት ግን ጠንካራ ጎኑ እንደሚያመዝን በጥናቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም የይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት በአብዛኛው ድክመቱ እንደሚያመዝን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል። ውህደቱን በተመለከተ ግን ጥሩ የሚባል አደረጃጀት እንዳለ የትንተናው ውጤት አመልክቷል። የመጻፍ ክሂል ትምህርት ሲደራጅ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋርም የጎን ለጎን ግንኙነት እንዲኖራቸውና ተዋህደው እንዲደራጁ የተደረገ በመሆኑ ውህደቱ የሰመረ ነው። ከዚህ ግኝት በመነሳትም አጥኚው የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ሲደራጁ በበቂ መጠን ተደጋግመው እንዲደራጁ፣ ተደጋግመው የመጡ ይዘቶችም ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅ፣ ከቅርብ ወደሩቅ እንዲሁም አስፈላጊነታቸውን ታሳቢ በማድረግ እንዲደራጁ፣ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችና አስማሚዎች በመጽሐፍ ዝግጅት ወቅት፣ መምህራንም ትምህርቱን ክፍል ውስጥ በሚያቀርቡበት ወቅት የአደረጃጀት መርሁን ታሳቢ እንዲያደርጉ የመፍትሄ ሀሳቦችን ሰንዝሯል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ እንደትምህርት መስጫም ሆነ እንደጥናት መስክ ሁኖ ለበርካታ ዓመታት አገልግሎት ሰጥቷል፤ እየሰጠም ይገኛል። እንደጥናት መስክ ሲሰጥ ተቀዳሚ ግቦቹ አራቱን የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች (የሥነልሳንና የሥነጽሑፍ እውቀቶች) ለማዳበር ነው። ዓላማዎቹ ግባቸውን ይመቱ ዘንድ ደግሞ በርካታ መሰናዶዎች ያስፈልጋሉ። ከእነዚህ ውስጥ ግንባር ቀደሞቹ የትምህርት ይዘቱ እና የማስተማር ስነዘዴው በቂ እውቀትና ክህሎት ያለው መምህር፣ በወጉ የተዘጋጁና ችግራቸው በየጊዜው የሚታረሙ መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህር መምሪያዎችና መርሀትምህርቶች፣ ወዘተርፈ ያስፈልጋሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሌሎቹ ትልቁን ድርሻ የሚይዙት መማሪያ መጻሕፍት ናቸው። ምክንያቱም ከማስተማሪያ ዘዴውም ሆነ ከመምህሩ ችግር ቢኖር ተማሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍትን በሚገባ በማንበብ ክፍተቱን መድፈን ይችላሉና።

የመማሪያ መጻሕፍት አዘገጃጀት በቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ምሁራን ይገልጻሉ (Cunningsworth 1995 and Ur 2006)። በሚዘጋጁበት ወቅት በትምህርትነት የሚመረጡ ይዘቶች ተገቢ በሆነ አቀራረብና ለተማሪዎቹ ቀላልና አስፈላጊ በሆነ አደረጃጀት መሆን ይኖርበታል። ይህ ከሆነ ተማሪው የሚማረውን አስተማሪውንም የሚያስተምረውን በውል ይረዳሉ፤ ወላጁም ቢሆን ልጁ ስለምን እንደሚማር መረጃ በመማሪያ መጻሕፍቱ ማወቅ ይችላል።

መማሪያ መጻሕፍት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይህን ያህል ቦታ የሚሰጣቸው ከሆኑ ደግሞ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች እንዲሁም የሥነልሳንና የሥነጽሑፍ እውቀት ይዘቶች በትኩረት መመረጥ ብሎም በጥሩ ሁኔታ መቅረብና መደራጀት ይኖርባቸዋል። በተለይም ደግሞ ለመጻፍ ክሂል ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ ውስብስብና በመጨረሻ የምንለምደው ክሂል የመጻፍ ክሂል በመሆኑ ነው (Richards 1990፣100)። ክሂሉ እንደቃላዊ ክሂሎች

(ማዳመጥና መናገር) በኢመደበኛ ዐውድ የምናዳብረው ባለመሆኑ በትምህርት ቤት በልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። እንደዚሁም ሁሉ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በደንብ ሊደራጅ ይገባል።

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የመጻፍ ትምህርት እንደይዘት ቢካተትም የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ግን ዝቅተኛ እንደሆነ በመስኩ ላይ ጥናት ያደረጉ አጥኚዎች ያስረዳሉ (ጽጌ 1992፣ አስቴር 1998 እና አስቻለው 2000)። ለዚህም እንደምክንያት በመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት የሚገኙ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ችግር (ተሻለ 2005 እና ጽጌ 1992)፣ የማስተማሪያ ስነዘዴ አመራረጥና አተገባበር ክፍተት (አስቻለው 2000)፣ የመምህሩ የማስተማር ብልሀት እንዲሁም የተማሪውን ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን (አስቴር 1998) የመጻፍ ክሂል ደረጃ ዝቅተኛ እንዲሆን እንደሆኑ ገልጸዋል።

ተሻለ እና ጽጌ የመጻፍ ክሂል አቀራረብና አደረጃጀት ለመጻፍ ክሂል ደረጃ ዝቅ ማለት ምክንያቶች ናቸው ካሉ፣ ከ2004 ጀምሮ እስካሁን አገልግሎት እየሰጡ ባሉ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ምን ያክል እንደተቀረፈ መፈተሽ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት አጥኚ መነሻ የሆነው ባስተማረባቸው ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክህሎት አናሳ መሆን ነው። ይህ ደግሞ የትምህርት ግብን ሊያሳካ ስለማይችል በጥናት ችግሩ መለየትና አስፈላጊ የሆነ ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ጥናት ለማጥናት አነሳስቶታል። አጥኚው በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ለ11 ዓመታት አገልግሏል። በአገልግሎት ዘመኑም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ሲያጤን በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ታዝቧል። ተጠባቂው ችሎታና የተማሪዎቹ የክህሎት ደረጃ ሲቀራረቡ አላየም። ትምህርት ሚኒስቴር (2004) በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ ዘገባዎችን፣ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን፣ ወዘተርፈ በጥሩ ሁኔታ እንዲጽፉ በመርሀ ትምህርቶቹ ይገልጻል። ሆኖም ግን የተማሪዎቹ ችሎታ ሲጤን በመርሀ ትምህርቶቹ ከሰፈሩት የብቃት ደረጃዎች ጋር በጣም የተራራቀ ነው (አስቴር 1998 እና አስቻለው 2000)።

ይሄ ጉዳይ የቅርብ ተማሪዎችን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ሥነ-ጥበብና ትምህርት ሚኒስተር (1956፣ 57) ላይ የአማርኛ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርትን ዓላማ ሲገልጽ "ማናቸውም ተማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ሲጨርስ በመጠኑ በንግግርም ይሁን በጽሁፍ አሳቡን ለመግለጽ እንዲችል ማስተማር ነው፡፡" ይላል፡፡ 1990 ላይ ያለው ሰነድም ሲታይ ተማሪው የቋንቋውን አወቃቀር ሥርዓት ጠብቆ ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ ሪፖርትና የመሳሰሉትን የመጻፍ አቅም እንዲኖረው ማድረግ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ወደ አተገባበሩና ውጤቱ ሲመጣ ግን የሚታየው እውነት ለየት ያለ እንደነበር ባየ (1987)፣ ተስፋየ (1986) እንዲሁም አምሳሉና ደምሴ (1982) ያስረዳሉ፡፡ የመጻፍ ክሂል በተጠበቀው ደረጃ ላይ ላለመገኘቱ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የመማሪያ መጻሕፍት አዘገጃጀት ነው (ተሻለ 2005 እና ጽጌ 1992)፡፡ በዝግጅት ደግሞ የይዘትና የትምህርት ልምድ መረጣ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ታሳቢ ይደረጋሉ፡፡ ስለሆነም የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት የተደራጁበትን መንገድ መገምገም ለክሂሉ እድገት የራሱን አስተዋጽዖ ስለሚያበረክት የተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍትን የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁበትን መንገድ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓብይ ዓላማ ዳር ለማድረስ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላዎች ይካተታሉ፡፡

- በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶችን ተከታታይነት መፈተሽ፣
- የይዘቶቹንን የትምህርት ልምዶቹን ተለጣጣቂነት መመርመር እና
- የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ተግባራት ያላቸውን ውህደት መፈተሽ የሚሉት ንዑሳን ዓላዎች ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ለመምህራን፣ ለአጥኝዎች፣ ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ወይም አሻሻዮች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

- የክፍል ደረጃዎቹን የሚያስተምሩ መምህራን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የመጻፍ ክሂል የተደራጀበትን መንገድ በማጤን ለተማሪዎቹ በሚመች መንገድ ለማቅረብ አቅጣጫ ያመላክታል፡፡
- በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጻሕፍትን ለሚያዘጋጁ ወይም ለሚያሻሽሉ ሰዎች የበፊቶቹ የክሂሉ ይዘቶች ያለባቸውን ጥንካሬና ድክመት ተመልክተው ጠንካራ ጎኖችን እንዲያስቀጥሉና ድክመቶቹን እንዲያሻሽሉ ፍንጭ ይሰጣቸዋል፡፡
- በመጻፍ ክሂል አደረጃጀትና መሰል ርዕሰ ጉዳዮች ሰፊ ጥናት ማጥናት ለሚፈልጉ አጥኝዎች ተጨማሪ መረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎት እየሰጡ ባሉት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው የቀረቡ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች የተደራጁበትን መንገድ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ አደረጃጀታቸውን ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት አንጻር ይመለከታል፡፡ በሌሎች የክሂላት ተግባራት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ ይዘቶች ቢኖሩም ጥናቱ እነኚህን ተግባራት አይመለከትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህን ጥናት ለማጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገለው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ሆኖም ግን አጥኚው ካለው የማየት ውስንነትና በስራ ላይ ሆኖ ጥናቱን ስላደረገው ከመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ጥናቱ መጠነኛ ውስንነት ሊኖርበት ይችላል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የመጻፍ ክሂል ምንነት

ክሂሉን በተመለከተ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ግን የሚቀራረቡ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። የአብዛኛዎቹ ማዕከላዊ ሀሳብ መጻፍ ድምጽን፣ ቀለምን ወይም ቃልን ወክለው በሚመጡ ትዕምርቶች አማካይነት ሀሳብን፣ መልዕክትን፣ መረጃንና ስሜትን ለመጻፍ ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ማስተላለፍ እንደሆነ ከሚያነሱት ሀሳብ መረዳት እንችላለን (Harmer 1991 እና Widdowson 1978)። በአንድ ቋንቋ ውስጥ በርካታ ድምጾች የሚገኙ ሲሆን ቋንቋው የጽሕፈት ሥርዓት ያለው ከሆነ እነዚያን ድምጾች ሊወክሉ የሚችሉ የተለያዩ ምልክቶች ይኖሩታል። እነዚያ ምልክቶች ሥርዓት ባለውና ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ተደራጅተው ሲቀርቡና መተላለፍ የተፈለገው ነገር ሲተላለፍባቸው ጽሕፈት ይባላል።

Janet (2003) የመጻፍ ክሂል አዲስ ግኝትን የመፈለግና ትርጉም የመስጠት ችሎታ መሆኑን በመግለጽ ያስረዳሉ። የJanet ሀሳብ የመጻፍን ክሂል በትዕምርቶች አማካይነት ሀሳብን ከማስተላለፍ ባለፈ ሌላ ትርጉም እንዳለው የሚያመላክት ነው። ይህ ሀሳብ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን የበድሉ (1996)ን ሀሳብ እንመልከት። እንደ በድሉ ገለጻ በመጻፍ ሂደት ውስጥ የማሰብ ብልሀት፣ መላ የመምታትና ግምት የመስጠት ችሎታ አለ። መጻፍ ምልክቶችን ከመለየት ባሻገር ማስተላለፍ የምንፈልገውን ነገር መሸከም የሚችሉ ቃላትን የመምረጥ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓረፍተነገሮችን ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ የማቀናጀት፣ ሀሳብን የማፍለቅና የማደራጀት ሥራም ነው። ይህንኑ ሀሳብ ማረው (1996) ይጋሩታል። መጻፍ በትዕምርቶች አማካይነት ድምጾችን ከወከልን በኋላ የሚያቆም ክንውን እንዳልሆነና የማቀናጀት ሥራንንም እንደሚያካትት ያስረዳሉ። አቀነጻጀቱም ድምጾች ተቀናጅተው ቀለማትን፣ ቀለማትም ቃላትን፣ ቃላትም ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን፣ ዓረፍተነገሮችም አንቀጾችን እንዲሁም አንቀጾችም የተሟላ ድርሰትን እንዲያስገኙ በሥርዓት መቀናጀት ይኖርባቸዋል።

የመጻፍ ክሂል ድምጾችን ወክለው በሚመጡ ትዕምርቶች አማካይነት ሀሳብን፣ ስሜትን ወይም መልዕክትን በጽሑፍ አማካኝነት የሚተላለፉበት ክሂል እንደሆነ ቀደም ባሉት

ገለጻዎች ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ስንመለከተው ለመልመድ አስቸጋሪው፣ የቃላት መረጣ፣ የሀሳብ አፍልቆት የአቀነጃጀት እና መሰል እውቀቶች የሚያስፈልጉት እንዲሁም አዲስ ግኝት የመፈለግና ትርጉም የመስጠት ችሎታ የሚያስፈልገው ክሂል መሆኑን እንረዳለን፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም የመጻፍ ክሂል ትምህርት በጽሑፍ ሀሳብን በማስፈር ሂደት የሚታዩ ይዘቶችን አካቶ የሚይዝ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ሌሎች ክሂላትን በማስተማር ሂደት ክሂሉን መጠቀም በሚያስፈልግበት አጋጣሚ ቢኖርም ጥናቱ የሚመለከተው ለመጻፍ ክሂል መለማመጃነት ብቻ ታልመው የተዘጋጁ ይዘቶች ብቻ በግምገማው ውስጥ ተካተዋል፡፡

## 2.2 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች

የቋንቋ ትምህርት ግቡን ይመታ ዘንድ በውስጡ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ያስፈልጋሉ፡፡ የትምህርት ይዘቶች የምንላቸው እውቀትን፣ ችሎታን፣ አመለካከትን ወይም እሴትን ለማስተማር የሚያገለግሉ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ጭብጦችና የመሳሰሉት እንደሆኑ WordPress (2016) ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም አንድን በቋንቋ ትምህርት ክሂልንም ሆነ የእውቀት ዘርፍን ለማስተማር የሚያገለግሉና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡ ማስታዎሻዎች፣ የተለያዩ አስረጅዎች፣ መለማመጃዎችና የተለያዩ ተግባራት በይዘት ሥር ይካተታሉ፡፡

በዚህ ጥናትም የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ ይዘቶች “ድርሰት መጻፍ” እና “የአጻጻፍ ሥርዓት” በሚሉ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎ የሚታይ ነው፡፡ ድርሰት በመጻፍ ሥር ሀሳብ አፍልቆ መጻፍን የሚመለከቱ ይዘቶች የሚካተቱ ሲሆን ዝርዝሮቹም ከተለያዩ ምንጮች ማስታዎሻ በመያዝ ጽሑፍ መጻፍ፣ የማነቃቂያና የቅስቀሳ ጽሑፍ መጻፍ፣ በድርጊት ቅደም ተከተል ድርሰት መጻፍ፣ ለጭውውት የሚሆን ጽሑፍ መጻፍ፣ ከግጥም የተረዱትን ሀሳብ ወደጽሑፍ መቀየር፣ አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ፣ ደብዳቤ መጻፍ፣ ቃለ ጉባኤ መጻፍ የሚሉት ይካተታሉ፡፡ በአጻጻፍ ሥርዓት ውስጥ ደግሞ ድርሰት በመጻፍ ሂደት ማዳበር ያላባቸው ንዑሳን ክሂሎችንና እውቀቶች የሚያዳብሩባቸው ሲሆን ዝርዝሮቹ ስርዓተ ነጥብ፣ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት፣ ስዕላዊ መግለጫን ወይም ሰንጠረዥን ወደጽሑፍ መቀየር፣ ጽሑፍን

ወደሰንጠረዥ መቀየር፣ የግል አስተያየትንና ሀቅን መለየት፣ የአንቀጽ ባህሪያትና ቅርጽ፣ ሀሳብን በራስ አባባል መግለጽ፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ፣ የተጓደሉ ጽሑፎችን ማሟላት፣ ለቃላት ፍች መስጠት እና ዓረፍተነገር ማዋቀር ወይም መመስረት የሚሉት ናቸው፡፡

የመጻፍ ክሂል ይዘቶቹም በሚመረጡበት ወቅት በርካታ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በበርካታ ምሁራን ተቀባይነት ያገኙት ለተማሪዎቹ ሳቢና የመማር ፍላጎታቸውን የሚቀሰቅሱ ጉዳዮችን በጥንቃቄ መምረጥ፣ የመጻፍ ክሂላቸውን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ተግባራትን መምረጥ፣ ከልጆቹ ትምህርታዊና ባህላዊ ዳራ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን እንዲለማመዱባቸው ማሰናዳት እና ተግባራቱን ለማከናወን የሚቀርቡ አስረጅዎችና ማሳያዎች እውነተኛ እንዲሆኑና በግልጽ ቋንቋ እንዲጻፉ ጥንቃቄ ማድረግ የሚሉት ናቸው (Arias 2007 and Prince Edwared Island 2008)፡፡

ፍላጎት አንድን ጉዳይ የሚያንቀሳቅስ ሞተር ነው፡፡ በምንሰራው ነገር ላይ ፍላጎት የማይኖረን ከሆነ ውጤታማነቱ ያጠራጥራል (Kenneth 1997)፡፡ ስለዚህ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች በሚመረጡበት ወቅት ፍላጎት አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚስብ ጉዳይ ለማቅረብ ደግሞ የተሻለው መንገድ ለራሳቸው የቀረቡ ጉዳዮችን ማካተት እና ከባህላዊ ዳራቸው ጋር ግንኙነት በሚኖራቸው ጉዳዮች ላይ ማተኮር የተሸለው መንገድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእድሜ ደረጃቸውና ትምህርታዊ ዳራቸውም ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በመጻፍ ሂደት ሀሳቡም ሆነ የአጻጻፍ ስልቱ ሲኖረን ነው ጥሩ ጽሑፍ መጻፍ የምንችለው፡፡ የማናውቀውና የተወሳሰበ ጉዳይ ላይ በቂ ሀሳብ አፍልቀን ላንጽፍ እንችላለን፡፡ ሀሳቡ ኑሮን ያን ሀሳብ ለማስፈር የሚያስችል የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት የማንችል ከሆነና የቋንቋ አጠቃቀማችን ላይ ችግር ካለ ተመሳሳይ ችግር ይከሰትብናል፡፡

የተማሪዎችን የተለያዩ ዳራዎች ከማሟላትና ፍላጎትና ከመቀስቀስ ባሻገር ይዘቶቹ ወይም የትምህርት ልምዶቹ የታለመውን የትምህርት ዓላማ የሚያሳኩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የትምህርቱ ዓላማ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አመዛዛኝ ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ ከሆነና የመረጥነው የትምህርት ልምድ ግን ትረካ ነክ ጽሑፍ ከሆነ የትምህርቱ ዓላማ ላይሳካ

ይችላል። ለልጆቹ ታሪክ ነክ ጽሑፍ ሊስባቸውና ፍላጎታቸውን ሊቀሰቅስ እንደሚችል ቢታመንም የተመረጠው ጉዳይ ታላሚውን ዓላማ እስካላሳካ ድረስ ተገቢነት ይጎድለዋል። ስለዚህ የተማሪዎችና እድሜና የክፍል ደረጃ ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ጉዳዮች ሊካተቱ ይገባል። በተጨማሪም ትክክለኛነታቸው በመረጣው ላይ ትልቅ አስተዋጽዖ ይፈጥራል። በይዘትነት የሚቀርቡ ማስታዎሻዎችና መልመጃዎች ትክክለኛ ካልሆኑ ተማሪዎቹ የተሳሳተ ትምህርት ሊቀስሙ ይችላሉ። አስረጅዎቹ ወይም ናሙና ጽሑፎቹ የሚያነሱት ጉዳይም እውነተኛ ካልሆነ ተማሪዎቹ ለነገሮች የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል።

## 2.3 የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች አደረጃጀት

አደረጃጀት የሚባለው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከተመረጡ በኋላ የሚኖራቸውን የአሰዳደርና አቀነጃጀት ሥርዓት ነው። አቀነጃጀቱ የይዘቶችን የድግግሞሽ መጠን፣ እርስ በርስ የሚኖራቸውን ትስስርና የሚቀርቡበትን ቅደም ተከተል ይመለከታል (Tyler 1949)። በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶችም በተገቢው ቅደም ተከተልና በበቂ ድግግሞሽ ሊቀርቡ ይገባል። ይዘቶቹ ወይም የትምህርት ልምዶቹ ሲደራጁ በዋናናት መሰረት የሚያደርጉት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ አድርጎ ማቅረብን ነው። በወጉ የተደራጀ የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች ለመማር ለመምህሩም ለማስተማር አያስቸግርም፤ በተጨማሪም የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካትም ያግዛል።

የመጻፍ ክሂልም ከቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች ውስጥ እንደመካተቱ መጠን በውስጡ የሚኖሩ ይዘቶች በወጉ ሊደራጁ ይገባል። ይዘቶቹ እርስ በርስ በሚኖራቸው ትስስር የሚመጣው ባለፈው ጉዳይ ላይ እየተመሰረተና እየተለጣጠቀ ያለፈውም ቀጣዩን ጉዳይ ለማስቀጠል ምቹ እየሆነ ሊቀርብ ይገባል። ይህን አስመልክቶ ጽጌ (1992)፣ Ponsor እና Rodensky (1986)ን ዋቢ በማድረግ የይዘቶች አደረጃጀት በይዘቶች መካከል መተጋገዝና ህብረት እንዲኖር ማድረግ እንደሆነ ያስረዳሉ። የሚደጋገፉትና ህብረትን የሚፈጥሩት ደግሞ ጥሩ የሆነ የአደረጃጀት መርህን መከተል ሲቻል ነው። የአደረጃጀት መርሁ የተሳካና የተስተካከለ የሚሆነው የአሰዳደራቸውን ቅደም ተከተል ለመወሰን፣ የድግግሞሽ መጠናቸውን ለማወቅና ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን

ግንኙነት ለማጤን እንዲመች የይዘቶችን የክብደት ደረጃ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ድረጃቸው ከይዘቶቹ ክብደትና ቀለት ወይም ተጨባጭነትና ረቂቅነት አንጻር ሊሆን ይችላል፡፡

የይዘቶችን ያደረጃጀት መርህ ሊወስኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ዋነኞቹ ለትምህርትነት የሚቀርበው ክሂል ወይም የእውቀት ዘርፍና በውስጡ የሚካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ባህርይ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂልም በተመሳሳይ የሚከተላቸው ያደረጃጀት መርሆች አሉት፡፡ የመጻፍ ክሂል ትምህርት በአብዛኛው የሚቀርበው በትግበራ እንደመሆኑ መጠን ትምህርቱ እንዲሰጽ የሚጽፉበት መንገድና የሚጽፉበት ጉዳይ ተደጋግሞ ሊመጣ ይገባል፡፡ ተደጋግሞ የመጣው ጉዳይም ከቅርብ ወደሩቅ፣ ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅ ሊዋቀር ይገባዋል (Richard, Underhile and Andrew 2007)፡፡ ከዚህም ባሻገር የሚኖረው አደረጃጀት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ወይም ከሌሎች ክሂላት ጋር ተቀናጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከተነሱት ጉዳዮች አንጻር የይዘቶች የአደረጃጀት መርህ ተዋረዳዊና ጎናዊ አደረጃጀት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ (Richard, Underhile and Andrew 2007, Steve 2009, Tyler 1949, Cunnungsworth 1995 and Nunan 1992)፡፡

ተዋረዳዊ አደረጃጀት (Vertical Organization) በአንድ የትምህርት አይነት በአንድ ክሂል ወይም የእውቀት ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የሚዋቀሩበትን መንገድ የሚመለከት የአደረጃጀት መርህ ነው፡፡ አደረጃጀቱም በአንድ መማሪያ መጽሐፍ ወይም በአንድ እርከን ብሎም በተለያዩ እርከኖች ውስጥ ባሉ ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ማስተማሪያነት በሚያገለግሉ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ሊከናወን ይችላል፡፡ ይዘቶቹ በመማሪያ መጽሐፉ ወይም መጻሕፍቱ ውስጥ የሚደጋገሙበትን መጠን፣ የአሰዳደራቸውን ሁኔታና ባህርይ፣ ሲደጋገሙ ሊኖራቸው የሚችለውን የስፋትና የጥልቀት መጠን እንዲሁም እርስ በርስ የሚኖራቸውን ትስስር ይመለከታል፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የተለያዩ ጉዳዮች መደገም ባለባቸው መጠን ተደጋግመው ሲቀርቡና አንዱ ይዘት ከአንደኛው ይዘት ጋር እየተዛመደና እርስ በርሱ እየተሳሰረ ቢቀርብ ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ተመራጭ መንገድ እንደሆነ General Practice Supervisors Australia (2014) ያስረዳሉ፡፡

ጎናዊ አደረጃጀት (Horizontal Organization) በአንድ የትምህርት አይነት የሚገኙ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከሌላ የትምህርት አይነት ይዘቶች ጋር እያዛመዱ ማዋቀርን የሚመለከት ነው (General Practice Supervisors Australia 2014 and Cunnungsworth 1995)፡፡ ይህ የአደረጃጀት መንገድ በቋንቋ ትምህርት ከይዘቶች ይልቅ የትምህርት ልምዶችን የሚመለከት ነው፡፡ ለምሳሌ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ስንፈልግ ተማሪዎችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለአንዱ ጉዳይ እንዲጽፉ ብናደርጋቸው የቋንቋ ትምህርት ከታሪክ ትምህርት ጋር ተዛምዶ ስለቀረበ አደረጃጀቱ ጎናዊ ይባላል፡፡ ለቋንቋ ትምህርት የኢትዮጵያ ታሪክ የትምህርት ልምዱ ነው፡፡ የክሂሉ ይዘት ደግሞ አንቀጽ መጻፍ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በአደረጃጀቱ ውስጥ አዛማጅ ሆኖ የቀረበው የትምህርት ልምዱ ነው፡፡

ይህ የአደረጃጀት መርህ በተለያዩ ደረጃዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶችና ልምዶች ተዋህደው እንዲቀርቡና ጣምራ ውጤት እንዲያስገኙ የሚያደርግ ነው፡፡ ከአደረጃጀት መርሆች ውስጥ ውህደት በዚህ ሥር ይካተታል፡፡ በጎናዊ አደረጃጀት ሥር ደግሞ ተከታታይነትንና ተለጣጣቂነት ይካተታሉ፡፡

### 2.3.1 ተከታታይነት (Continuity)

WordPress (2016) ተከታታይነት (Continuity) በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ የሚገኝ አንድ የትምህርት ይዘት ተማሪዎቹ በደንብ እስኪካኑት ወይም እስኪያውቁት ድረስ ተደጋግሞ መምጣት እንዳለበት የሚያሳይ የአደረጃጀት መርህ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ክሂሎችም ሆኑ የእውቀት ዘርፎች ይካተታሉ፡፡ ክሂሎቹም ሆኑ የእውቀት ዘርፎቹ በውስጣቸው የተለያዩ ይዘቶችን አካተው ይይዛሉ፡፡ ተከታታይነት የሚባለውም ከሚካተቱ ይዘቶች ውስጥ አንዱን በመጽሐፉ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ አካቶ ማቅረብ ነው፡፡

በመጻፍ ክሂል ውስጥ በድርሰት መጻፍና በአጻጻፍ ሥርዓት ሥር በርካታ ይዘቶች ይካተታሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በብዛት ተደጋግመው የሚመጡት አንቀጽ መጻፍ፣ ድርሰት መጻፍ፣ ዓረፍተ ነገሮችን ወይም ወይም አንቀጾችን አርሞና አቃንቶ መጻፍ፣ በተሰጠ ኀይለቃል አማካኝነት መዘርዝራዊ ዓረፍተ ነገሮችን በማሟላት የተሟላ አንቀጽ መጻፍ፣ ሥርዓተ ነጥብን በአግባቡ መጠቀም፣ የተጀመረን ሀሳብ ቋጭቶ መጻፍና

የመሳሰሉት ናቸው። ለአብነት ያህል አንድ የትምህርት ይዘት ወስደን ተከታታይነትን እንመልከት። የትምህርት ይዘቱ አንቀጽ መጻፍ ቢሆን ለተማሪዎቹ የተስተካከለ አንቀጽ ለመጻፍ የአንድ ቀን ትምህርት ሊበቃቸው አይችልም። መጻፍ ሊዳብር የሚችለው ባላሰለሰ ጥረትና በልዩ ትጋት ነው (ደረጀ 2007)። ስለዚህ ትምህርቱ አንዴ ብቻ ቀርቦ ከተማሪዎቹ የተዋጣለት የብቃት ደረጃ መጠበቅ ይከብዳሉ፤ ልዩ ተሰጥዖ እስካልታከለበት ድረስ። ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ቅርጹንና የትምህርት ልምዱን በመቀያየር ደጋግሞ ማቅረብ ይገባል።

አንድ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሲካተተት የመደጋገም እድል ከሌለውና አንዴ ብቻ ቀርቦ የሚቀር ከሆነ የመረሳት እድሉ ሰፊ ይሆናል። በአንጻሩ በተለያየ የጥልቀትና የስፋት ደረጃ እየተደጋገመ የሚቀርብ ከሆነ የመስረጽ እድሉ የሰፋ ይሆናል። በእርግጥ "ሁሉም ይዘቶች ይደጋገሙ፤ ሁሉም ይዘቶች በእኩል መጠን ይደጋገሙ" አይባልም። አንዳንዱ ይዘት አንዴ ብቻ ቀርቦ ባይደገም በትምህርቱ ላይ ተጽዕኖ ላይፈጥር ይችላል፤ በአንጻሩ አንዳንዱ ይዘት ደግሞ ተደጋግሞ ካልመጣ በቀር ተማሪዎቹ በውል ላይረዱት ይችላሉ። ስለሆነም በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶችን ከመደጋገማችን በፊት የይዘቶችን ባህርይና የክብደትና የቅለት መጠን ከትምህርት ቤቱ አካባቢና ከተማሪዎቹ አንጻር በደንብ መመርመር ያስፈልጋል።

የድግግሞሽ መጠናችንም ሊወስኑ የሚችሉት ዐበይት ጉዳዮች የይዘቱ ባህሪና ተማሪዎች ስለይዘቱ ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ነው። የይዘቱ ባህሪ የክብደትና የቅለት ደረጃውን ወይም ውስብስብነቱን የሚመለከት ሲሆን ቀላል የሚባል ይዘት ከሆነ የተወሰነ ድግግሞሽ ወይም ከባድ ከሆነ ደግሞ በርካታ ድግግሞሽ ያስፈልገዋል። ተማሪዎቹ ስለይዘቱ ያላቸው ግንዛቤ ደግሞ ይዘቱን በሚመለከት በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ወይም በቀደሙት የትምህርት ደረጃዎች የተማሩት ከመሆንና ካለመሆን አንጻር ይታያል። ለምሳሌ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር በሚያገለግሉ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ  የፊደል አጻጻፍን (ፍደላን) የሚመለከት ይዘት ቢቀርብ ተደጋግሞ መምጣት አያስፈልገውም። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ባለፉባቸው የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተድምጻዊ ግንዛቤዎችን በብዛት ስለሚማሩና በደንብም ልምምድ ያደርጉባቸዋልም ተብሎ ስለሚጠበቅ ተደጋግሞ ላይቀርብ ይችላል።

በዚህ የአደረጃጀት መርህ ሥር በዋናነት የሚታዩት የትምህርት ይዘቶች ቢሆኑም የትምህርት ልምዶችም ይዋቀራሉ (Taba 1962)፡፡ የመጻፍ ተግባራትን የሚያከናውኑት በትምህርት ልምዶች አማካኝነት እንደሆነ ቀደም ሲል በ2.3 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ተማሪዎችን በተለያዩ መልመጃዎች አማካኝነት የመጻፍ ክሂልን ስናስተምራቸው የሚጽፉበትን ጉዳይም ደጋግሞ ማቅረብ ለክሂሉ ውጤታማነት ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ ታሪክ ነክ ጽሑፎች እንዲጽፉ ተደርጎ ከሆነ በሌላ ጊዜም ታሪክ ነክ ጽሑፎችን እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ መልመጃዎችም በተመሳሳይ አስፈላጊ የሆነ የትምህርት ልምድ ድግግሞሽ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት የሚጻፍበት ጉዳይ በመለያየቱ የተነሳ የአጻጻፍ ቴክኒኮችም አብረው ሊቀየሩ ስለሚችሉ ነው፡፡ ስለአንድ ነገር ምንነት፣ አሰራርና የመሳሰሉትን ጉዳዮቸች በተመለከተ መጻፍ ሲፈለግ አንቀጻችን የሚስፋፉበት ስልት ስልት ብያኔያዊ፣ ታሪክ ነክ ጽሁፍ ሲሆን ተራኪ፣ ስለተለያዩ ጉዳዮች ምስስሎሽና ልዩነት በተመለከተ ለመጻፍ ማወዳደርና ማነጻጸር ይሆናል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ ሁሉንም አይነት ጽሑፍ በብቃት መጻፍ እንዲችሉ የተለያዩ የትምህርት ልምዶችም እንዲሁ ተደጋግመው መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡

የትምህርት ይዘቶችም ሆኑ የትምህርት ልምዶች ተግባራዊ የሚደረጉት በአንድ የክፍል ደረጃ ለማስተማሪያነት በሚያገለግል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ማስተማሪያነት በሚያገለግሉ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥም ይህ አደረጃጀት ይኖራል፡፡ ለምሳሌ “አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ” የሚል ንዑስ ይዘት ቢኖርና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቢካተት ተከታታይነት እንዲኖረው በአስረኛ ክፍል መማሪ መጽሐፍም ተካቶ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

በተከታታይነት የማደራጃ መርህ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው ይመጣሉ ሲባል በተመሳሳይ የክብደትና የቅለት ደረጃ ይደጋገማሉ ማለት አይደለም፡፡ ይህን አስመልክቶ Tyler (1949) በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው የሚመጡ ይዘቶች ተመሳሳይ ከመሆን ይልቅ በቅርጽና በክብደት ደረጃ መለያየት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ መንገድና በተመሳሳይ የክብደትና የቅለት መጠን ተከታትሎ የሚመጡ ከሆነ ተማሪዎችን ከማሰልቸቱም በላይ የታቀደው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ላይደርስ ይችላል፡፡

### 2.3.2 ተለጣጣቂነት (Sequence)

ተከታታይነት የይዘቶችን ተደጋግሞ መምጣት እየሰፉ መሄድን የሚያመለክት ሲሆን ተለጣጣቂነት ደግሞ ተደጋግመውና እየሰፉ የሚመጡ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የሚኖራቸውን ቅደም ተከተል፣ የክብደትና የቅለት፣ የተጨባጭነትና የውስብስብነት እንዲሁም የቅርበትና የርቀት ደረጃ የሚያመለክት ነው (Taba 1962 and WordPress 2016)። ተከታታይነትም ሆነ ተለጣጣቂነት የይዘቶችን ጎናዊ አደረጃጀት የሚመለከቱ እንደሆነ ቀደም ሲል ተወስቷል። ስለሆነም ዝምድናቸው በጣም የጠበቀ ነው። አንዱን ስናነሳ ሌላኛውም አብሮ ይነሳል። ሆኖም ግን ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት የላቀና የሰፋ የአደረጃጀት መርህ ነው። ተደጋግመው የመጡ ይዘቶች በምን ያህል የመስፋትና የመጥለቅ መጠን እንደቀረቡና ቅደም ተከተላቸውም የቱ ቀድሞ የቱ መከተል እንዳለበት ስለሚያሳይ የሰፋ የማደራጃ መንገድ ነው።

አደረጃጀቱ የትኛውን ቀድመው መማር እንዳለባቸውና ከቀደመው ጉዳይ ጋር እንዴት አድርገው ማያያዝ እንዳለባቸው ማስገንዘብ ስለሚችል ተማሪዎቹ ለሚማሩት ትምህርት ውጤታማነት ጉልህ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል። በተናጥል አንድን የትምህርት ይዘት ከማቅረብ ይልቅ ከሌሎች ይዘቶች ጋር በማዛመድ ቢቀርብ የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርግ ይታመናል። በተለጣጣቂነት መርህ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶችንም ሆነ የትምህርት ልምዶችን የምናዋቅር ከሆነ ግን የትምህርቱን ግብ ዳር ለማድረስ ትልቅ አስተዋጽዖ ለማበርከት ምቹ መሆኑን እንረዳለን።

ተለጣጣቂነት እንደ ተከታታይነት በአንድ የትምህርት ይዘት ላይ ብቻ አያተኩርም፤ ከዚያ ባለፈ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች የሚኖራቸውን ትስስርም ጨምሮ ይመለከታል (Nunan 1988)። አንድ የትምህርት ይዘት በተለጣጣቂነት ሲደራጅ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሲካተት የክብደትና የውስብስብነት መጠኑ በመጨመር መጠኑም እየበዛ ይመጣል። ለምሳሌ በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ ባለአንድ አንቀጽ ተራኪ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዝ ተግባር ቢኖርና በተከታታይነት መርህ በመጽሐፉ ሌላ ቦታ ላይ ይሄው ይዘት ተደግሞ ቢመጣ ለየት ያለ ቅርጽ ይኖረዋል። ታሪኩ ወሰብሰብ ያለ ሊሆንና ከአንድ አንቀጽ ወደሁለትና ሶስት አንቀጽ እንዲጽፉ የሚያዝ ይሆናል።

በተመሳሳይ አንድን ክሂል ወይም እውቀት ለማሳደግ የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችም የሚደራጁት በተለጣጣቂነት የአደረጃጀት መርህ ነው፡፡ ለምሳሌ በመጻፍ ክሂል ውስጥ የተለያዩ ሥርዓተ ነጥቦችን በጽሑፎች ውስጥ አካቶ መጻፍ፣ ያልተስተካከሉ ጽሑፎችን ማቃናት፣ የተጀመሩ አንቀጾችን መቋጨት፣ በገለጻ ሥልት የተስፋፋ አንድ አንቀጽ መጻፍ እና አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ የሚሉ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህን ይዘቶች እርስ በርስ ለማያያዝና ቅደም ተከተላቸውን በተጠይቃዊ መንገድ ለማዋቀር ተለጣጣቂነትን እንጠቀማለን፡፡ ቅደም ተከተልን በተመለከከተ የትኛው ይቅደም የቱ ይከተል የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የይዘቱን ባህሪ ተመልክተን የተለያዩ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ በምሳሌው ከላይ የቀረቡትን ይዘቶች ከአስፈላጊነት፣ ከቅለትና ክብደት አንጻር ስናደራጃቸው የሚኖራቸው ቅደም ተከተል ከላይ በሰፈሩበት ቅደም ተከተል ይሆናል፡፡ ከቅለት አንጻር ስንመለከተው ጽሑፍ ከመጻፍ ይልቅ በተጻፈ ጽሑፍ ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን ማሟላት የሚቀል ስለሆነ “የተለያዩ ሥርዓተ ነጥቦችን በጽሑፎች ውስጥ አካቶ መጻፍ” የሚለው ይዘት ቀድሞ ይመጣና ሌሎችም እንደጽሑፎቹ ብዛት ተከታትለው ይመጣሉ፡፡ ከአስፈላጊነት አንጻርም ቢሆን የተለያዩ ጽሑፎን ለመጻፍ አርትዖት ማድረግና ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀም ቀድሞ መማሩ ስለሚያስፈልግ ሥርዓተ ነጥቦችን ማስገባትና ማስተካከያ መስጠት ቀድሞ መጥቶ ሌሎቹ ይዘቶች በየደረጃቸው ይከተላሉ፡፡

ተከታታይነት ላይ እንደተገለጸው በተለጣጣቂነትም ለአንድ የክፍል ደረጃ መማሪያነት ከሚያገለግል መማሪያ መጽሐፍ ባለፈ ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ማስተማሪያነት በሚያገለግሉ መማሪያ መጻሕፍትም ተለጣጣቂነት ይታያል (Tyler 1949)፡፡ በአንደኛው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የተካተተው የትምህርት ይዘት ወይም ይዘቶች ቀጥሎ በሚመጣው ወይም ቀድሞ በመጣው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ላይም ተከታትሎ ይመጣል፡፡ ከመደጋገሙ ጋር የይዘቱ ቅርጽና የክብደት ደረጃም አብሮ ይቀያየራል፡፡ በዚህ አደረጃጀት አነስ ባሉት የክፍል ደረጃዎች የማያስቸግሩና አጠር ያሉ የመጻፍ ተግባራት ቀርበው፣ ከፍ ላሉ ደረጃዎች ደግሞ ጠጠር ያሉና ረዘም ያሉ ጽሑፎችን እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ የትምህርት ልምዶችንም ቢሆን በተመሳሳይ ልክ እንደ ይዘቶች የክፍል ደረጃውን ጠብቀው በተጠቀሰው መንገድ ሊደራጁ ይገባል፡፡

የተለጣጣቂነትን የአደረጃጀት መርህ ተከትል ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶችን በቅደም ተከተል ለማዋቀር በርካታ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርብን የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ Okunloye (2014) ከቀላል ወደከባድ (easy to difficult)፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ (Concret-related to Abstract-related)፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ (known to unknown)፣ ከቅርብ ወደሩቅ (close at hand to far away)፣ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር (whole to parts)፣ ከዝርዝር ወደአጠቃላይ (parts to whole)፣ ከቀድሞ መጥ (prerequisite learnings) አንጻር እና ከጊዜ ቅደም ተከተል (Chronological order) አንጻር እንደሚደራጁ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ከመጻፍ ክሂል ጋር በቀጥታ ሊገናኙ የሚችሉ የማራጃ መንገዶች በተናጥል ቀርበዋል፡፡

## ሀ) ከቀላል ወደከባድ አደረጃጀት

አንድ ይዘት ተደጋግሞ ሲመጣ ወይም የተለያዩ ይዘቶች ተከታትለው ሲመጡ ቀድሞ መምጣት ያለበትን ለመወሰን እንደመመዘኛ ከሚወሰዱት ውስጥ አንዱ የይዘቶቹ የክብደትና የቅለት ደረጃ ነው፡፡ ለትግበራም ሆነ ለመረዳት የማያስቸግሩ ይዘቶች ቀድመው ይመጡና የክብደት ደረጃቸው እየጨመረ ሲመጣ ደግሞ ከቀላሉ እየተከተሉ ይቀርባሉ፡፡ ከባድ የሚባለው ይዘት ቀድሞ በመምጣት ቀላሉ የሚከተል ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን አክብደው በመመልከት ተስፋ እንዲቆርጡ ያደርጋቸዋል፡፡ የአንድን ይዘት ክብደትና ቅለት ሊወስኑ ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ የቃል አጠቃቀም፣ የሚጽፉት ጽሑፍ ርዝማኔ፣ የአገላለጥ ጥንካሬና ጽንሰ ሀሳባዊ ጥንካሬ የሚባሉት በመጻፍ ክሂል ውስጥ ይዘወተራሉ፡፡

በአስረጅነት ወይም በማስታወሻነት የቀረቡ ይዘቶች በቀላል ቋንቋና በተለምዷዊ አገላለጽ የሚገለጹ ከሆነ ይዘቶች ቀላል እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ በተግባራትም ወይም በመለማመጃዎችም ይሄው ነገር ይከሰታል፡፡ ዘይቤዎችንና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በማካተት ጽሑፍ እንዲጽፉ ቢታዘዙ ከተራው ጽሑፍ ከበድ ስለሚል መጀመሪያ አካባቢ መምጣት አይኖርበትም፡፡ ከጽሑፉ ርዝማኔ አንጻር ስንመለከተውም ደረጃ በደረጃ ብዛት ያላቸውን ጽሑፎች እንዲጽፉ የሚያዙ ይዘቶች መካተት እንደሚኖርባቸው ያስረዳል፡፡ በመጀመሪያ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ አዘን ከሆነ በሂደት ሁለትና ከዚያ በላይ አንቀጾችን እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡

ለምሳሌ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንድ አንቀጽ አስረጅ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዝ ይዘት ቢኖርና በመጽሐፉ ሌላ ቦታ ላይ ወይም ከፍ ባለው የክፍል ደረጃ ሌላ መጽሐፍ ላይ ደግሞ ባለሶስት አንቀጽ አስረጅ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዝ የተደገመ ይዘት ቢኖር ተለጣጣቂነታቸው የተስተካከለ ይሆናል፡፡ የተስተካከለ ያስባለውም ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀቱ ነው፡፡

## ለ) ከተጨባጭ ወደረቂቅ አደረጃጀት

በዚህ የማደራጃ መንገድ በዋናነት የሚደራጁት የትምህርት ልምዶች ናቸው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ከሚካተቱ የትምህርት ልምዶች ውስጥ ተጨባጭ ነገሮች ቀድመው መምጣት እንደሚኖርባቸው ይጠበቃል፡፡ ለተማሪዎች ስለማይታዩና ስረቂቅ ጉዳዮች ከመጻፍ ይልቅ ስለተጨባጭ ጉዳዮች መጻፍ ይቀናቸዋል፡፡ ተጨባጭ የምንላቸው ጉዳዮች በአይን የሚታዩ ብሎም በእጅ የሚዳሰሱ ሲሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ ሰዎች፣ እንስሳት፣ መልክዓምድራዊ ገጽታዎች፣ ወዘተ. ይካተቱበታል፡፡ ረቂቅ የምንላቸው ደግሞ የማይዳሰሱና የማይታዩ ጉዳዮችን የሚመለከት ሲሆን አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶች፣ እሳቤያዊ ነገሮች፣ ወዘተ. ያካትታል፡፡ ለምሳሌ የገጸባህርያትን ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታ እንዲጽፉ የሚያዝ ይዘት በመማሪያ መጽሐፍ ወይም መጻሕፍት የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ተከታትሎ ቢካተት ቀድሞ መምጣት ያለበት ስለውጫዊ ገጽታ እንዲጽፉ የሚያዘው ተግባር ነው፡፡ ውጫዊውን ገጽታ በሚገባ መግለጽ ሳይችሉ ስለማይታየው ነገር መጻፍ ይከብዳቸዋና፡፡

## ሐ) ከቅርብ ወደሩቅ አደረጃጀት

ሁሉም ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከተማሪዎቹ ልምድ፣ ዳራዊ እውቀት፣ ባህልና እድሜ እኩል ቅርበት የላቸውም (Okunloye 2014) ፡፡ በአደረጃጀት ወቅትም ለተማሪዎቹ ቅርብ የሆኑትን አስቀድመን እናመጣና ሌሎችን እናስከትላለን፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተደጋግመው ሲመጡ ወይም የተለያዩ የትምህርት ልምዶች ሲዋቀሩ ከቅርብ ወደሩቅ ሊደራጁ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረበው ይዘት አስረጅ ድርሰት መጻፍ ሆኖ ይዘቱን ለመተግበር የቡና አፈላልና የበርገር አዘገጃጀት የሚሉ የትምህርት ልምዶች ቢመረጡ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በአመዛኙ ሊቀርብ የሚችለው የትምህርት

ልምድ የቡና አፈላል የሚለው ነው፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መጽሐፍ ወይም መጻሕፍት ውስጥ በመጀመሪያ ቦታ መካተት ያለበት የቡና አፈላል ሆኖ የበርገር አዘገጃጀት የሚለው ደግሞ ይከተላል ማለት ነው፡፡

ቅርበትና ርቀትን ከዳራዊ እውቀት አንጻር ስንመለከተው ደግሞ በዋናነት የትምህርት ይዘቶችን ይይዛል፡፡ ተማሪዎቹ አንድን የትምህርት ይዘት ወይ ቀድመው የተማሩበት ወይም በህይወት ተሞክሯቸው የቀሰሙበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ከጉዳዩ ጋር በመጠኑም ይሁን በብዛት የተዋወቁበት አጋጣሚ ካለ ያ ጉዳይ ለተማሪዎቹ ቅርብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ለአስራሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ከልቦለድና ከሂስ ሊቀርባቸው የሚችለው ልቦለድ ነው፡፡ ስለሆነም ይዘቶቹ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሲካተቱ ቀድሞ መቅረብ ያለበት ልቦለድ ነው፡፡

ከሚታወቅ ወደማይታወቅ የሚባለው የማደራጃ መንገድም ከቅርብ ወደሩቅ ማደራጃ መንገድ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድ ይዘት ወይም የትምህርት ልምድ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በተለያዩ አጋጣሚዎች በተማሪዎች ዘንድ ሊታወቅ ይችላል፡፡ ጉዳዩን ሁሉም በእኩል መጠን ሊያውቁት እንደማይችሉ ቢታወቅም አብዛኛዎቹን ሊወክል ይችላል ብለን ልናምንበት የምንችለውን አስቀድመን ማምጣት እና ሌሎችንም እንደሚታወቁበት መጠን በቅደም ተከተል ማስከተል ያስፈልጋል፡፡ የቆጮ አዘገጃጀትና የእንጀራ አዘጀጃጀትን ብንወስድ በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ዘንድ ይታወቃል ተብሎ የሚጠበቀው የእንጀራ አዘገጃጀት ነው፡፡ በቅደም ተከተሉ ውስጥም ይህን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡

## መ) ከቀድሞ መጥ አንጻር

አንድን ይዘት ለመማር የሚያስፈልጉ ሌሎች ይዘቶች ይኖራሉ፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቀድመው መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡ በመጻፍ ክሂል ትምህርት ተማሪዎች አንድ የተቃናና የተስተካከለ ድርሰት እንዲጽፉ ቀድመው መማር ያለባቸው በርካታ የትምህርት ይዘቶች ይኖራሉ፡፡ የሥርዓተ ነጥቦች፣ የዓረፍተ ነገርና የአንቀጽ አወቃቀር፣ የሀሳብ አወቃቀር፣ ወዘተ. እውቀት የሌለው ተማሪ የተስተካከለ ጽሑፍ ለመጻፍ ይቸገራል፡፡

የትምህርት ልምዶችን ወይም ይዘቶችን ለህይወታቸው ከሚኖራቸው አስፈላጊነት አንጻርም ማየት ይቻላል፡፡ ለልጆቹ ህይወት የበለጠ አስፈላጊ ናቸው ብለን የምናምንባቸውን አስቀድሞ በማምጣት ሌሎችን ማስከተል የዚህ አደረጃጀት ሌላው መከሰቻ ነው፡፡ አስፈላጊነታቸው ከትምህርት ቤት ውጭ ካለው ሕይወት ባለፈ በትምህርት ህይወታቸው የሚጠቅሙትን ያካትታል፡፡

### 2.3.3 ውህደት (Integration)

ውህደት አደረጃጀቱ ከተለጣጣቂነትና ከተከታታይነት ለየት ያለ ሲሆን የሚመለከተውም በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ የሚኖረውን ዝምድና ነው (Taba 1962)፡፡ ስያሜው እንደሚያስረዳው በተለያዩ የትምህርት አይነቶች መካከል ያሉ ይዘቶችን አዋህዶ ማቅረብ ነው፡፡

ውህደት ከጎናዊ አደረጃጀት ጋር አብሮ የሚታይ ሲሆን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚኖረው ቦታ ጉልህ ነው፡፡ አንድ ተማሪ ጥሩ ጽሑፍ ጻፈ የሚባለው በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ብቻ ስለተጻፈ ሳይሆን ሁሉንም ጉዳይ አስመልክቶ መጻፍ ሲችል ነው፡፡ ታሪክ መጻፍና ሳይንሳዊ ጽሑፎችን መጻፍ መቻል የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በእርግጥ የሚጋሯቸው የአጻጻፍ ቴክኒኮች ሊኖሩ ቢችሉም የሚጻፍበት ርዕሰ ጉዳይ ሲለያይም በተመሳሳይ የመጻፊያ መንገዱም ይለያያል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ ውህደት አስፈላጊ ነው፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ተዛምደው ሲቀርቡ የአስተሳሰብ አድማሳቸውም በዚያው መጠን ይጎለብታል፡፡

## 2.4 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ የመጻፍ ክሂል በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ስላለው አደረጃጀት በተመለከተ አጥኚው ያጋጠመው ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎች ሲሆን እነሱም የጽጌ (1992) እና ኢትዮጵያ (2009) ናቸው፡፡ ሌላው ጥናት የአስቻለው (2000) ሲሆን ጥናቱ የመጻፍ ክሂልን አቀራረብ ይመለከታል፡፡

የመጀመሪያው ጥናት የጽጌ (1992) ሲሆን “ለጽህፈት ክሂል የተመረጡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል? አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 1987 ዓ.ም. ባዘጋጃቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (5-8) መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ የተደረገው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ከመማሪያ መጻሕፍቱ በሰነድ ፍተሻና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ፣ ከመጻሕፍት አዘጋጆች ደግሞ በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ በጥናቱ ውጤትም መማሪያ መጻሕፍቱ የተለጣጣቂነት መስፈርትን በአግባቡ የመጠቀም ችግር እንዳለባቸው አጥኝዋ አስረድተዋል፡፡ የጽጌን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የመጻፍ ክሂል አደረጃጀት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ የጽጌ ጥናት የተደረገው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ውስጥ ባሉ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን (ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል) ውስጥ ባሉ መማሪያ መጻሕፍት ላይ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መመሪያነት በተዘጋጁና አሁን አገልግሎት እየሰጡ ባሉ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ማተኮሩ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ሌላው ጥናት ደግሞ የአስቻለው (2000) ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን ርዕሱም “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጽህፈት ትምህርት አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍተሻ” የሚል ነው፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከመምህራንና ከተማሪዎች ነው፡፡ ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ የመጻፍ ክሂል ትምህርት በሚሰጥናቸው የተተኳሪ ተማሪዎች ክህለጊዜዎች ደግሞ በምልከታ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በጥናቱ ውጤት መምህራን የመጻፍ ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን በሚገባ እንዳልተጠቀሟቸው ተገልጿል፡፡ የአስቻለው ጥናት ከጽጌም ሆነ ከኢትዮጵያና ከዚህ ጥናት ጋር የሚያለያየው ዋና ጉዳይ ይዘቶችን ከመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከሚኖራቸው አቀራረብ ወይም አደረጃጀት በተለየ መልኩ በክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን አቀራረብ የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡ ከጥናቶቹ ጋር የሚያመሳስለው በመጻፍ ክሂል ይዘት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡

ሶስተኛው ጥናት የኢትዮጵያ (2009) ሲሆን ጥናቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ "በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋሉት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (ከ5ኛ-8ኛክፍል) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል?" የሚል ነው፡፡ ጥናቱን ለማጥናት የሰነድ ፍተሻ ከመማሪያ መጻሕፍቱ ቃለመጠይቅ ደግሞ ከአስማምቶ አዘጋጆች አድርገዋል፡፡ ከዚያም መረጃዎቹ ተተንትነው በአራቱም መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች የአደረጃጀት ችግር እንደታየባቸው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ጥናት ከጽጌ ጥናት ጋር በክፍል ደረጃ ተመሳሳይ መሆን ይመሳሰላሉ፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ደግሞ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ስላለው አደረጃጀት ላይ በማተኮሩና በአሁኑ ጊዜ አግልግሎት እየሰጡ ባሉ መማሪያ መጻሕፍት አደረጃጀት ላይ በማተኮሩ ያመሳስለዋል፡፡ ሆኖም የክፍል ደረጃቸውና የመረጃ ምንጮቻቸው መለያየታቸው ያለያያቸዋል፡፡

ሶስቱም ጥናቶች በመጻፍ ክሂል ዙሪያ የተደረጉ ናቸው፡፡ ሁለቱ በመማሪያ መጻሕፍት ላይ የተጠኑ ሲሆኑ አንዱ ግን ክሂሉ በክፍል ውስጥ የሚኖረውን አቀራረብ ይመለከታል፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ላይ የተሰሩት ጥናቶች በሙሉ የክሂሉን ይዘት አደረጃጀት ዳሰዋል፡፡ በመረጃ ምንጭነት ደግሞ ከሰነድ ፍተሻ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅንና መጠይቅን ተጠቅመዋል፡፡ የአስቻለው ጥናትም በክፍል ውስጥ አቀራረብ ጥናት እንደማድረጋቸው መጠን ከመጠይቅና ከቃለ መጠይቅ ባሻገር በምልከታ መረጃ ሰብስበዋል፡፡ ይህን ጥናት ከሶስቱም ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመጻፍ ክሂል ላይ ማተኮሩ ነው፡፡

በዚህ ክፍል ዳሰሳ ከተደረገባቸው ምርምሮች መካከል የአስቻለው (2000) ምርምር በመጻፍ ክሂል አቀራረብ ላይ ያተኩር እንጂ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያላቸውን አቀራረብ ስለማይፈትሽ ከዚህ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡ የጽጌ (1992) እና የኢትዮጵያ (2009) ጥናት ግን በመማሪያ መጻሕፍት ላይ ከማተኮራቸው በተጨማሪ በመጻፍ ክሂል የይዘት አደረጃጀቶች ላይ በማተኮራቸው ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስላቸውም ከመረጃ መሰብሰቢያ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አመራረጥ አኳያ ይለያያሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ጽጌ ግምገማ ያደረጉትም  የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ከመደረጉ (ከ2004 ዓ.ም.) በፊት በነበሩ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን መማሪያ መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ ይህም የዘመን

እርዝማኔና የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ መኖር አሁን አገልግሎት እየሰጡ ያሉ መማሪያ መጻሕፍት ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመገምገም ይህ ጥናት ተጠንቷል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጥናት ጋር መማሪያ መጻሕፍቱ ከታተሙበት (ሲታተሙ መነሻ ካደረጉበት ዓላማ) አንጻር ግምገማ የሚደረገው በተለያዩ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ ማለትም በዚህ ጥናት የተገመገሙ መማሪያ መጻሕፍት ከ2004 ጀምሮ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ መማሪያ መጻሕፍት ሲሆን የኢትዮጵያ ደግሞ በ2008 ዓ.ም ለመጻፍና ለማንበብ ክሂሎች ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በማመን ማሻሻያ በተደረገባቸው መማሪያ መጻሕፍት (የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን) ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም የዚህ ጥናት መማሪያ መጻሕፍት የተዘጋጁት በትምህርት ሚኒስተር ሲሆን የኢትዮጵያ ደግሞ አማራ ክልል በቅድሚያ አዘጋጅቷቸው የደቡብ ክልል በራሱ መማር ማስተማር ዐውድ አስማምቶ ያዘጋጃቸው ናቸው፡፡ ይህም ከዚህ ጥናት ጋር ያለያያቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ንድፍ በዋናነት ያተኮረው በገላጭ ጥናት ላይ ነው፡፡ ይህ ጥናት ንድፍ አይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) ጋር የተሳሰረ ሲሆን መረጃዎችን ገለጻዊ በሆነ አቀራረብ በማቅረብ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ጥናትም በምዕራፍ ሁለት ላይ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና አደረጃጀቶች ለመፈተሽ የሚያስችሉ ንድፈሀሳቦችን በመመርኮዝ የተለያዩ አስረጅዎችን በማቅረብ በመጻሕፍቱ ውስጥ ያለውን እውነታ በገለጻ መልክ የሚያቀርብ ነው፡፡ ለዚህም ገላጭ ጥናትን መጠቀም የተሻለ መንገድ በመሆኑ ጥናቱ ይህን ንድፍ ተጠቅሟል፡፡

መረጃዎችን በገለጻ መልኩ በማቅረብ የሚታወቀው የጥናት ዘዴ አይነታዊ የጥናት ዘዴ እንደሆነ ተገልጧል፡፡ ጥናቱም የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶችን መፈተሽ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ዘዴው ተመራጭ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ መረጃዎች የተተነተኑት በገለጻ እንደመሆኑ መጠን ይህን ዘዴ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ከመጠናዊ ዘዴ የጸዳ ነው ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ በቁጥርና በመቶኛ የተገለጹ ቁጥር ነክ መረጃዎች ስላሉ መጠናዊ ዘዴ በመጠኑ በጥናቱ ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት የተደረገው በ2003 ዓመተ ምህረት ታትመው በ2004 ዓመተ ምህረት አገልግሎት መስጠት የጀመሩ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ በመሆኑ በምረጃ ምንጭነት ያገለገሉትም ሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሆኖም ግን አስፈላጊ መረጃዎችን ለመውሰድ ለክፍል ደረጃዎቹ የተዘጋጁ የመምህር መምሪያዎቹ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህን ጥናት ለማጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡

በሰነድ ፍተሻ የተፈተሹት በ2003 ዓመተ ምህረት ታትመው በ2004 ዓመተ ምህረት አገልግሎት መስጠት የጀመሩ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ መጻሕፍቱ ዋና የመረጃ ምንጭ ሲሆኑ በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶችን ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነት እና ከውህደት አንጻር እንዴት እንደተደራጁ ለመፈተሽና ለመገምገም አገልግለዋል፡፡

የመረጃ አሰባሰቡም በመጀመሪያ በሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ታስበው የተዘጋጁ "ጽሕፈት" በሚል ርዕስ ስር ያሉ ይዘቶችና ይዘቶቹ የቀረቡባቸው የትምህርት ልምዶች ተለይተው ወጥተዋል፡፡ ከዚያም የጥናቱን ንዑሳን ዓላማዎች እና በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በተነሱ ንድፈ ሀሳቦች መነሻነት ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትን እና ውህደትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በየፈርጅ በየፈርጃቸው ተከፋፍለዋል፡፡ ከዚያም ለትንታኔ እንዲያመቹ የተጠቀሱ ጉዳዮችን ሊገልጹ የሚችሉ አስረጅዎች ከፊሎቹ በጽሑፍ ከፊሎቹ ደግሞ ከ"ሶፍትኮፒ" ተቆርጠው በመውጣት በቅደም ተከተል ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁበትን መንገድ በመፈተሽ መገምገም ነው፡፡ ይህን ጥናት ለማጥናት መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሰነድ ፍተሻ እንደመሆኑና የተሰበሰቡ መረጃዎችም ከቁጥር ይልቅ በአይነት በአይነት አንደመቅረባቸው መጠን በአብዛኛው አገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡ ሁለቱም የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ይከተላሉ፡፡ ምክንያቱም በርካታ መረጃዎች የሚቀርቡት በገለጻ በመሆኑ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ቀላል ስታትስቲካዊ መረጃዎች ተካተዋል፡፡ እነዚህ ቁጥር ነክ ስታትስቲካዊ መረጃዎች (የተለያዩ ይዘት ድምሮችና የይዘቶቹ የመቶኛ ስሌቶች) በሰንጠረዥ እየተደራጁ በመጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴ ቀርበዋል፡፡

ትንታኔው ተከፋፍሎ የቀረበው የጥናቱን ንዑሳን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም እንዳስፈላጊነታቸው ንዑሳን ዓላማዎችን መሰረት ባደረጉ ርዕሰጉዳዮች ለተፈላጊው ዓላማ ውለዋል፡፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ያላቸውን አደረጃጀት ለመፈተሽ እና ጥንካሬና ጥንካሬና ድክመታቸውን ለመለየት ያስችላሉ የተባሉ አስረጅዎች ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍና ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የበለጠ የሚያስረዱት እየተመረጡ ተካተዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁበትን መንገድ መፈተሽ ነው፡፡ በውስጡም በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከተዋረዳዊ (ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት) እና ከጎናዊ አደረጃጀት (ከውህደት) አኳያ ተፈትሸዋል፡፡ ለጥናቱም አገልግሎት ላይ የዋሉት የመማሪያ መጻሕፍት ሲሆኑ በሰነድ ፍተሻ መረጃ ተሰብስቦባቸዋል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትኖ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል፡፡ አተናተኑ የተከፋፈለው የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## 4.1 ከተከታታይነት አንጻር

ተከታታይነት ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከሚደራጁባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በመጻሕፍቱ የሚካተቱ ይዘቶቹም ሆኑ የትምህርት ልምዶቹ በተማሪዎቹ እንዳይረሱ፣ በተለያዩ መንገዶች እንዲረዷቸውና በተነሳው ጉዳይ ላይ ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምር ሲባል ተደጋግሞ የሚቀርብበት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ በስፋት ተብራርቷል፡፡ በመሆኑም በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች በምን ያህል መጠን ተደጋግመው እንደመጡና ተደጋግመው የመጡትም በምን ያህል ስፋት እና ጥልቀት እንደሆነ በዚህ ክፍል ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል በመጻሕፍቱ ዳራዊ መግለጫ ላይ እንደተብራራው በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ በአስር ምዕራፎች 32 ያህል ይዘቶች፣ እንዲሁም በአስረኛ ክፍል በስድስት ምዕራፎች 21 ያህል ይዘቶች ተካተዋል፡፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችን የድግግሞሽ መጠን ለመፈተሽ እንዲያመች በሁለት ማዕቀፍ ተከፍለው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው “ድርሰት መጻፍ” የሚል ሲሆን በተለያዩ ጉዳዮች፣ የተለያዩ ዐውዶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሰሩ የሚያዙ ይዘቶችን የሚያካትት ነው፡፡ ከአንቀጽ ጀምሮ እንዲጽፉ የሚያዙ ተግባራትን በሙሉ ያካትታል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ “የአጻጻፍ ሥርዓት” የሚል

ነው፡፡ ይሄም ጥሩ ጽሑፍ እንዲጽፉ የሚያደርጉ የተለያዩ ሥርዓቶችን፣ ደንቦችን የሚያሳውቁና የሚያለማምዱ ይዘቶችን የሚያካትት ነው፡፡ ለምሳሌ ሥርዓተ ነጥቦች፣ የአንቀጽ አጻጻፍ ሥርዓቶችና የመሳሰሉት ተካተውበታል፡፡ በቀጣዩ ሰንጠረዥ የዘጠነኛ ክፍል የድርሰት መጻፍ ይዘቶች፣ ብዛታቸውና የሚገኙበት ገጽ ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡-** የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የድርሰት መጻፍ ይዘቶች ተከታታይነት

| ዝርዝር ይዘቶች | ዘጠነኛ ክፍል የይዘቶች ብዛት | | የአስረኛ ክፍል የይዘቶች ብዛት | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ከተለያዩ ምንጮች ማስታዎሻ በመያዝ ጽሑፍ መጻፍ | 3 | 37.5 | 5 | 45.5 | 8 | 42.1 |
| የማነቃቂያና የቅስቀሳ ጽሑፍ መጻፍ | - | - | 2 | 18.2 | 2 | 10.5 |
| በድርጊት ቅደም ተከተል ድርሰት መጻፍ | 1 | 12.5 | - | - | 1 | 5.3 |
| ለጭውውት የሚሆን ጽሑፍ መጻፍ | 1 | 12.5 | - | - | 1 | 5.3 |
| ከግጥም የተረዱትን ሀሳብ ወደጽሑፍ መቀየር | 1 | 12.5 | - | - | 1 | 5.3 |
| አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ | - | - | 1 | 9.1 | 1 | 5.3 |
| ደብዳቤ መጻፍ | 2 | 25 | 2 | 18.2 | 4 | 21.1 |
| ቃለ ጉባኤ መጻፍ | - | - | 1 | 9.1 | 1 | 5.3 |
| ድምር | 8 | 100 | 11 | 100 | 19 | 100 |

**ማሳሰቢያ፡-** መቶኛው የተሰላው ከድርሰት መጻፍ ይዘቶች ድግግሞሽ ብዛት አንጻር ነው፡፡ ይዘቶቹ ደግሞ ከድግግሞሻቸው አንጻር 8 በመሆናቸው መቶኛውም ይህን ቁጥር ታሳቢ አድርጓል፡፡

ከሰንጠረዥ ሁለት ላይ እንደምንመለከተው ድርሰት መጻፍ በሚል ማዕቀፍ ውስጥ ከተካተቱ ይዘቶች ውስጥ በብዛት በዘጠነኛ ክፍልም ሆነ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በብዛት ተደጋግሞ የተካተተው "ከተለያዩ ምንጮች ማስታዎሻ በመያዝ ጽሑፍ መጻፍ" የሚለው ነው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ድርሰት መጻፍ በሚል ክፍል ውስጥ ከተካተቱት 8 ይዘቶች ውስጥ 3ቱ ከተለያዩ ምንጮች ማስታዎሻ በመውሰድ ጽሑፍ መጻፍ የሚሉ ተግባራት ናቸው፡፡ ማለትም 37.5% ያህሉ በተጠቀሰው ይዘት ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ ከ11 ይዘቶች መካከል 5 (45.5%) ያህሉ በተመሳሳይ ከተለያዩ ምንጮች በተወሰዱ ማስታወሻ ጽሑፍ የሚጻፍባቸው ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት በብዛት ተደጋግሞ የመጣው "ደብዳቤ መጻፍ" የሚለው ሲሆን በዘጠነኛ ክፍል ከ 8ቱ የድርሰት መጻፍ ይዘቶች ውስጥ 2 (25%) ያህሉ በአስረኛ ክፍል ደግሞ ከ11 የድርሰት መጻፍ ይዘቶች ውስጥ 2 (18.2%) ያህሉ በደብዳቤ መጻፍ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል በድርጊት ቅደም ተከተል ድርሰት መጻፍ፣ ለጭውውት የሚሆን ጽሑፍ መጻፍ እና ከግጥም የተረዱትን ሀሳብ ወደጽሑፍ መቀየር የሚሉ ይዘቶች ያልተደገሙ (አንዳንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ) ይዘቶች ሲሆኑ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ግን አልተካተቱም፡፡ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ የማነቃቂያና የቅስቀሳ ጽሑፍ መጻፍ 2 (18.2%) ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ፣ አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ እና ቃለ ጉባኤ መጻፍ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ (9.1%) ብቻ የቀረቡ ይዘቶች ሲሆኑ በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ግን ያልተካተቱ ይዘቶች ናቸው፡፡

የሰነድ ፍተሻው መረጃ እንደሚያሳየው በድርሰት መጻፍ ስር ከቀረቡ ስምንት ይዘቶች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ ይዘቶች ከዘጠነኛ ክፍል ሁለት ከአስረኛ ክፍል ደግሞ ሶስት ይዘቶች ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ይዘቶች ግን ያለምንም ድግግሞሽ እንዳልቀረቡ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በክለሳ ድርሳናት ተከታታይነት በሚለው ርዕስ ውስጥ የተገለጸው ሀሳብ ግን ከዚህ የሚጻረር ነው፡፡ የምሁራኑ ሀሳብ በመማሪያ መጽሀፍ ወይም መጻሕፍት የሚካተቱ ይዘቶች ተማሪዎቹ እንዲለማመዷቸውና በደንብ እንዲካኗቸው መደጋገም አለባቸው ይላልና፡፡ ስለሆነም በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሁሉም የድርሰት መጻፍ ይዘቶች በየክፍል ደረጃዎቹ በብዛት እንዳልተደጋገሙ በተመሳሳይ በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ

ያሉ አብዛኛዎቹ ይዘቶች በአስረኛ ክፍል እንዳልተካተቱና በአስረኛ ክፍል የተካተቱ አብዛኛዎቹ ይዘቶችን በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ እንደሌሉ ያሳያል፡፡ ይህም ይዘቶቹ የቀጣይነትና የድግግሞሽ ችግር እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ የአጻጻፍ ሥርዓትን የመመለከቱ ተግባራት በሰንጠረዥ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡-** የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶች ተከታታይነት

| ዝርዝር ይዘቶች | ዘጠነኛ ክፍል የይዘቶች ብዛት | | የአስረኛ ክፍል የይዘቶች ብዛት | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶ ኛ | በቁጥር | በመቶ ኛ | በቁጥር | በመቶ ኛ |
| ስርዓተ ነጥብ | 2 | 8.3% | - | - | 2 | 5.7 |
| አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት | 7 | 29.2 % | 1 | 9.1 | 8 | 22.9 |
| ስዕላዊ መግለጫን ወይም ሰንጠረዥን ወደጽሑፍ መቀየር | - | - | 1 | 9.1 | 1 | 2.9 |
| ጽሑፍን ወደሰንጠረዥ መቀየር | 1 | 4.2% | 1 | 9.1 | 2 | 5.7 |
| የግል አስተያየትንና ሀቅን መለየት | - | - | 2 | 18.2 | 2 | 5.7 |
| የአንቀጽ ባህሪያትና ቅርጽ | 2 | 8.3% | 1 | 9.1 | 3 | 8.6 |
| ሀሳብን በራስ አባባል መግለጽ | 1 | 4.2% | - | - | 1 | 2.9 |
| አስተዋጽኦ መንደፍ | 1 | 4.2% | - | - | 1 | 2.9 |
| ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ | 3 | 12.5 % | 2 | 18.2 | 5 | 14.3 |
| የተጓደሉ ጽሑፎችን ማሟላት | 2 | 8.3% | 1 | 9.1 | 3 | 8.6 |
| ለቃላት ፍች መስጠት | 3 | 12.5 % | 1 | 9.1 | 4 | 11.4 |
| ዓረፍተነገር ማዋቀር ወይም መመስረት | 2 | 8.3% | 1 | 9.1 | 3 | 8.6 |
| ድምር | 24 | 100% | 11 | 100 | 35 | 100 |

**ማሳሰቢያ፡-** መቶኛው የተሰላው ከአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶች ድግግሞሽ ብዛት አንጻር ነው፡፡ ይዘቶቹ ደግሞ ከድግግሞሻቸው አንጻር 24 በመሆናቸው መቶኛውም ይህን ቁጥር ታሳቢ አድርጓል፡፡

ከሰንጠረዥ 3 ላይ እንደምናየው የአጻጻፍ ሥርዓትን የሚመለከቱ በዘጠነኛ ክፍል 24 ይዘቶች በአስረኛ ክፍል ደግሞ 11 ይዘቶች በመጻሕፍቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ከሁሉም ይዘቶች ውስጥ ተደጋግሞ የመምጣት እድል የገጠመው “አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት” የሚለው ነው፡፡ ከሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ ከተካተቱ 35 ይዘቶች ውስጥ 8 (22.9%) ያህል ጊዜ በድግግሞሽ ተካቷል፡፡ ከስምንቱ ውስጥ ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሰባቱ ቀሪው አንዱ ደግሞ አስረኛ ክፍል ላይ የተካተተ ነው፡፡ ቀጥሎ በብዛት የተደጋገመው ይዘት “ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ” ሲሆን በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 5 ቦታዎች ላይ ተደጋግሟል፡፡ በተናጥል ዘጠነኛ ክፍል ላይ ከቀረቡ 24 የአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶች ውስጥ 3 (12.5%) ያህሉ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ከቀረቡ 11 የአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶች ውስጥ 2 (18.2%) ያህሉ ተደጋግመው የቀረቡ ናቸው፡፡

ለቃላት ፍች መስጠት በዘጠነኛ ክፍል 3 (12.5%) ጊዜ በአስረኛ ክፍል ደግሞ 1 (9.1%) ጊዜ ብቻ ቀርቧል፡፡ የተጓደሉ ጽሑፎችን ማሟላት በዘጠነኛ ክፍል 2 (8.3%) ጊዜ ሲደጋገም በአስረኛ ክፍል ግን አንድ ጊዜ ቀርቦ አልተደገመም፡፡ በሌላ በኩል የአንቀጽ ባህሪያትና ቅርጽ በዘጠነኛ ክፍል 2 (8.3%) ያህል በአስረኛ ክፍል አንዴ ቀርቦ አልተደገመም፡፡ እንዲሁም ዓረፍተ ነገርን ማዋቀር ወይም መመስረት በዘጠነኛ ክፍል 2 (8.3%) ያህል ተደግመ ሲቀርብ አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ግን አልተደገመም፡፡ ጽሑፍን ወደሰንጠረዥ መቀየር በዘጠነኛም ሆነ በአስረኛ ክፍል ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል፡፡

ቀሪዎቹ የአጻጻፍ ሥርዓትን የሚመለከቱ ይዘቶች በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ወይም በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ብቻ የተካተቱ እንጅ አንዱ በሌላኛው ውስጥ የተካተተ አይደለም፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ተካተው በአስረኛ ክፍል ውስጥ የሌሉ ይዘቶች ስርዓተ ነጥብ 2 (8.3%)፣ ሀሳብን በራስ አባባል መግለጽ እና አስተዋጽኦ መንደፍ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል፡፡ በአስረኛ ክፍል ውስጥ ተካተው በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ የሌሉት ደግሞ ስዕላዊ መግለጫን ወይም ሰንጠረዥን ወደጽሑፍ መቀየር (1/9.1%) እና የግል አስተያየትንና ሀቅን መለየት (2/18.2%) ናቸው፡፡

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ “የአጻጻፍ ሥርዓት” ይዘቶችና የተደራጁበትን መንገድ ከተከታታይነት አንጻር ሲታይ ልክ እንደ “ድርሰት መጻፍ” ይዘቶች ተመሳሳይ ችግር

ታይቶባቸዋል፡፡ የዘጠነኛ ክፍል የአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶችን ከአስረኛ ክፍል የአጻጻፍ ሥርዓት ይዘቶች አንጻር ሲታዩ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ከሶስት ይዘቶች በስተቀር የድግግሞሽ መጠናቸው ቢለያይም ተደጋግመዋል፡፡ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ግን ከሁለት ይዘቶች በስተቀር የተደገመ ይዘት የለም፡፡ ይህም የድግግሞሽ መጠናቸው ዝቅ ያለ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በአንደኛው የክፍል ደረጃ የተካተተው ይዘት በሌላኛው የክፍል ደረጃ ላይ በቀጣይነት መካተትን በተመለከተ ደግሞ ከ12 ይዘቶች ውስጥ 7 (58.3%) ያህል ይዘቶች ብቻ በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 5 (41.7%) ያህሉ ወይ በዘጠነኛ ወይም በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ የተካተቱ ናቸው፡፡ ይህም ተከታታይነቱን የደከመ ያደርገዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በስፋት ያየነው የይዘቶችን ተከታታይነት ነው፡፡ በመቀጠል የትምህርት ልምዶቹ ተከታታይነትን በተመለከተ ከሰነድ ምርመራ የተገኘው መረጃ ቀርቧል፡፡ አብዛኛዎቹ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ልምዶች መሰረት አድርገው የቀረቡት በምዕራፉ ርዕስና በምዕራፉ ውስጥ በተካተተው ምንባብ ጉዳይ ላይ እንደሆነ በመጻሕፍቱ ዳራዊ ቅኝት ላይ ተገልጧል፡፡ ይህም ማለት በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ ይዘቶች ከተካተቱ በምዕራፉ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት ልምድ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም የትምህርት ልምዶቹ ተደጋግመው የመጡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤትም ያሳየው ይህንኑ ነው፡፡

በመጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን የያዙ የትምህርት ልምዶች ቋንቋን የሚመለከቱ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች፣ ሥነጽሑፋዊ ጉዳዮች፣ አካባቢያዊ ጉዳዮች፣ መገናኛ ብሁኀን፣ ባህላዊ ጉዳዮች፣ ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ አመለካከትን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ ሥራን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በተጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ የተለያዩ ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን ተከታታይነቱ ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ በብዛት ተደጋግመው የመጡት ሥነጽሑፋዊና ቋንቋ ነክ የትምህርት ልምዶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ በአንደኛው የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ልምዶች በሌላኛው የክፍል ደረጃም ተካተው የተገኙት ሥነጽሑፋዊና ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሌሎቹ ጉዳዮች ወይ በአስረኛ ክፍል ውስጥ ብቻ ወይም በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ብቻ የተካተቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የቋንቋን ምንነትና አገልግሎት የሚመለከት የትምህርት ልምድ ቀርቦ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ የቋንቋን ጥንተ አመጣጥ የሚገልጽ የትምህርት ልምድ ተካቷል፡፡ ይህም ቋንቋ ነክ ጉዳዮች በየክፍል ደረጃውም በድግግሞሽ መቅረባቸውን ያሳያል፡፡ በአንጻሩ አካባቢያዊ ጉዳይና መገናኛ ብዙሀንን የሚመለከቱ ጉዳዮች በዘጠነኛ ክፍል ላይ ብቻ ሲገኙ ባህላዊ፣ ጤናንና አመለካከትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ደግሞ በአስረኛ ክፍል ብቻ የተካተቱ ናቸው፡፡ ይህም በየክፍል ደረጃው ያለ ድግግሞሽ ጥሩ ቢሆንም ሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ግን በጥምረት ሲታዩ የትምህርት ልምድ ተከታታይነት ችግር እንዳለባቸው የሰነድ ፍተሻው ያሳያል፡፡

እንዳጠቃላይ ከይዘቶች ተከታታይነት አንጻር በዘጠነኛ ክፍልም ሆነ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች የተከታታይነት መርህን በተገቢው መልኩ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዳልተደራጁ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ የይዘቶቹ ተከታታይነት በየክፍል ደረጃውም ሆነ በክፍል ደረጃዎች መካከልም ተመሳሳይ ችግር ታይቷል፡፡ የትምህርት ልምዶች ድግግሞሽ አንጻር ግን በየክፍል ደረጃዎች ያሉ የትምህርት ልምዶች በበቂ መጠን ተደጋግመው የተደራጁ ሲሆን በዘጠነኛ ክፍል ያሉት የትምህርት ልምዶች በአስረኛ ክፍል ላይ ከመደገም አንጻር ግን ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡

## 4.2 ከተለጣጣቂነት አንጻር

በጎናዊ አደረጃጀት መርህ በቋንቋ ትምህርትነት የተመረጡ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተደጋግመው መቅረብ እንዳለባቸውና ድግግሞሻቸውም መስፋትና መጥለቅ እንዳለበት በተደጋጋሚ ተወስቷል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ በተለጣጣቂነት የሚነሳው ጉዳይ ደግሞ ተደጋግመው የመጡ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ወይም የተለያዩ የመጻፍ ክሂልና የትምህርት ልምዶች የሚቀርቡበትን ቅደም ተከተል የሚያመለክት ሲሆን አደረጃጀቱም ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅ፣ ከቅርብ ወደሩቅ እና በጣም ከሚያስፈልጉት ወደ በመጠኑ የሚያስፈልጉት የሚደራጁበትን

የሚያሳይ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተብራርቷል፡፡ በዚህ ክፍልም የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ከተጠቀሱት ጉዳዮች አንጻር ተፈትሸው ቀርበዋል፡፡

### 4.2.1 ከቀላል ወደከባድ አደረጃጀት

ተደጋግመው የሚመጡ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ መደራጀት እንዳለባቸው ቀደም ሲል ተገልጧል፡፡ ከዚህ ማደራጃ መንገድ አንጻር የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍትን ለመፈተሽ ይመች ዘንድ በተከታታይነት ላይ በቀረበው መንገድ የደርሰት መጻፍ ተግባራትን ከአጻጻፍ ሥርዓት በመለየት ቀርቧል፡፡ ስለሆነም በድርሰት መጻፍ ስር የተዘረዘሩት ተግባራት ከቀላል ወደከባድ መደራጀታቸው የሚገመገመው ከሌላ ድርሰት መጻፍ ተግባር ጋር እንጅ ከአጻጻፍ ሥርዓት ተግባራት ጋር አይሆንም ማለት ነው፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የመጻፍ ክሂልና የትምህርት ልምዶች በየደረጃው በከፊል ከቀላል ወደከባድ የተደራጁ ሲሆኑ በከፊል ደግሞ ከከባድ ወደቀላል ተደራጅተዋል፡፡ ለዚህም እንደአስረጅ ከአጻጻፍ ሥርዓት ውስጥ አያያዦችን እንመልከት፡፡

**ቅንጫቢ 1፡-** ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አያያዥን በተመለከተ ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

**ጀ. ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተዘረዘሩ ዓረፍተነገሮችን አያይዙ፣**

1. ሀ. መበለጸግ የሚቻለው ጠንክሮ በመሥራት መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡
   ለ. መበልጸግ የሚቻለው በወሬ አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡
2. ሀ. እውቀት የሚዳብረው በሒደት ነው፡፡
   ለ. ክሂል የሚዳብረው በሒደት ነው፡፡

**ፎ. የሚከተሉትን አጣማሪዎች (አያያዦች) በመጠቀም የተጣመሩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ**

1. ነገር ግን    2. ስለዚህ    3. በዚህም ሳቢያ

(ዘጠነኛ ክፍል፣ ገጽ 65)

በቅንጫቢ 1 ላይ እንደምናየው ሁለት አያያዥን የሚመለከቱ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ተግባር አያያዦችን በመጠቀም የተሰጡ ዓረፍተ ነገሮችን ማዋቀር ሲሆን ሁለተኛው ተግባር ደግሞ አያያዦች ተሰጥተው ሀሳብ በማመንጨት ዓረፍተ ነገሮችን ማዋቀር ነው፡፡ አያያዥን መጨመር ለተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገር ከማዋቀር ይልቅ የቀለለ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም ቦታዎች ላይ ያሉ አያያዦችም ሆኑ ሌሎች የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ ተደራጅተዋል ማለት አይደለም፡፡ ይህንን ሀሳብ ቀጣዩ አስረጅ ያስረዳዋል፡፡

**ቅንጫቢ 2፡-** ከዘጠነኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* አያያዥን በተመለከተ ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

**፭. በሚቀጥለው ታሪክ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ ዓረፍተነገርን ከዓረፍተነገር፣አንቀጽን ከአንቀጽ ያያያዙ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ ለዩ፡፡**

"በአሥራ ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ገደማ፣ የሱዳን ጦር ምዕራባዊውን የኢትዮጵያን ድንበር እያለፈ ዘረፋ በማካሄድ የአካባቢውን ሕዝብ በጣም ያስቸግር ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ የወገን ጦር (የኢትዮጵያ ጦር) ከጎንደር በመንቀሳቀስ፣ በሀገሩ ላይ የተቃጣውን ሕገ ወጥ ድርጊት

(ዘጠነኛ ክፍል፣ ገጽ 137)

በቅንጫቢ 1 ላይ ያሉት ሁለት ተግባራት ከቅንጫቢ 2 ላይ ካሉ ተግባራት አንጻር ስንመለከታቸው ከበድ የሚሉ ናቸው፡፡ አያያዦችን በጽሑፍ ውስጥ ለይቶ ማውጣት አያያዦችን ከራስ አዕምሮ ፈልጎ በማምጣት ሊሆኑ የሚችሉ አያያዦችን መርጦ ጽሑፍን ከማዋቀር እና ከተሰጡ ዓረፍተ ነገሮች አያያዦችን መርጦ ዓረፍተ ነገሮችን ከማዋቀር የሚቀል ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ቀድሞ የመጡት ግን በቅንጫቢ አንድ ላ ያሉ ተግባራት ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ አገባብ አደረጃጀቱ ከቀላል ወደከባድ የአደረጃጀት መርህን የተከተለ አይደለም፡፡

በተመሳሳይ በድርሰት መጻፍ ስር የቀረቡ ተግባራትም ከቀላል ወደከባድ ያመደራጀት ችግር ታይቶባቸዋል፡፡ በዘጠነኛ ክፍል በምዕራፍ ስምንት በገጽ 137 ላይ አንድ ታሪካዊ

ጽሑፍ ቀርቦ ቃልን ከቃል፣ ዓረፍተነገርን ከዓረፍተነገር፣ አንቀጽን ከአንቀጽ ያያያዙ ቃላትን በጥንድ ሆነው እንዲለዩ የሚያዝ ተግባር ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያ የቀረበው ተግባር በግል እንዲሰራ የታዘዘ ከመሆኑም በላይ ሀሳቦችንና አያያዦችን ከአፅምሯቸው ማፍለቅ ስለሚኖርባቸው በምዕራፍ ስምንት ከቀረቡ ተግባራት ይልቅ ከበድ ይላሉ፡፡ ከምንባብ ላይ አያያዦችን መለየት ከሚታየው ነገር ላይ መለየት በመሆኑና በጥንድም የሚሰራ ተግባር እንደመሆኑ ለተማሪዎቹ አይከብድም፡፡ ስለሆነም በዚህ አገባብ ከከባድ ወደቀላል አደረጃጀትን የተከተለ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህም የአደረጃጀት መርሁ የማይፈቅደው ነው፡፡

በአስረኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* የተካተቱ ይዘቶች እና የትምህርት ልምዶችን በተመለከተ ከዘጠነኛ ክፍል በተሻለ መልኩ ጥሩ የሆነ አደረጃጀት አለው፡፡ አብዛኛዎቹ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁት ከቀላል ወደከባድ ነው፡፡ ለዚህም አስረጅ እንዲሆን "ማስታዎሻ ከተለያዩ ምንጮች በመውሰድ ጽሑፍ መጻፍ" በሚል ይዘት ተደጋግመው የመጡ ሁለት ይዘቶችን እንመልከት፡፡

**ቅንጫቢ 3፡-** ከአስረኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ማስታዎሻ በመውሰድ ጽሑፍ መጻፍን በተመለከተ ከቀረበው ተግባር ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

> ፬. በተሰያዩ ቡድኖች ሆናችሁ በትምህርት ቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ የህዝብ ቤተመጻሕፍት በመሄድ ቀጥሉ የሚቀርብላችሁን የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያን ተከትላችሁ ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች ላይ ስለ ቋንቋ ባህሪያት አጫጭር ማስታወሻዎችን በመያዝ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ አቀናብራችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

(አስረኛ ክፍል፣ ገጽ13)

**ቅንጫቢ 4፡-** ከአስረኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ ማስታዎሻ* በመውሰድ ጽሑፍ *መጻፍን* በተመለከተ ከቀረበው ተግባር ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

**፩. የምርምራዊ የንባብ ዓይነት በመጠቀም ማህበረሰብና ጤናን የተመለከቱ ጽሑፎችን በሚገባ እንብባችሁ ጠቃሚ ሐሳሞቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ::**

(አስረኛ ክፍል፣ ገጽ57)

በአስረኛ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተቀንጭበው የወጡ ተግባራትን ስናጤን መጀመሪያ ላይ የመጣው ተግባር በቡድን የሚሰራ ሆኖ ከተለያዩ ጽሑፎች አንብበው ማስታዎሻ በመያዝ ጽሑፍ እንዲጽፉ የሚያዝ ነው፡፡ በዚህ ይዘት የቀረበው የትምህርት ልምድ የቋንቋ ባህሪያት ሲሆን ለጉዳዩ እንግዳ እንዳልሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ በሁለተኛነት የቀረበው ተግባር ደግሞ በግል የሚሰራ ሆኖ የትምህርት ልምዱ ማህበረሰብና ጤና የሚልና የንባብ አይነቱ ደግሞ የምርምራዊ ንባብ እንዲከተሉ የሚያዝ ነው፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ከትምህርት ልምድ አንጻር ከዘጠነኛ ክፍል ላይ የተነሳ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ለተማሪዎቹ የንባብ አይነቱ ስላልተገለጸ በተመቻቸው መንገድ አንብበው ማሳታዎሻ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛው በግል መቅረቡ፣ የትምህርት ልምዱም ለተማሪዎቹ እንግዳ ከመሆኑና ከንባብ አይነቶች ውስጥ የማመዛዘን ችሎታ የሚጠይቀውን የንባብ አይነት መመረጡ ከመጀመሪያ ተግባር ከበድ ያለ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ተግባራት ከከባድ ወደቀላል የተደራጁ እንደሆኑ አመላካች ነው፡፡

ሁሉም የአስረኛ ክፍል የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ የተደራጁ እንዳልሆኑ ተገልጿል፡፡ ለዚህም አስረጅ እንዲሆን ቀጣዮችን ተግባራት እንመልከት፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ በአራተኛው እና በስምተኛው ምዕራፎች ውስጥ “የቅስቀሳና የመነቃቂያ ጽሑፍ መጻፍ” የሚሉ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ ገጽ 54 ላይ ያለው ተግባር “ማህበሰብና ጤናን በተመለከተ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር በጽሑፍ አዘጋጁና በክፍል ውስጥ በንባብ አቅርቡ፡፡” የሚል ሲሆን በስምንተኛው ምዕራፍ በገጽ 112 ላይ የተካተተው ተግባር ደግሞ ተከታዩ ተግባር ቀርቧል፡፡

**ቅንጫቢ 5፦** ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የምዕራፍ ስምንት የመጻፍ ክሂል ተግባራት

፩. ከሴቶች ጉዳይ ተጠሪ፣ ከሴት ተማሪዎች ክበብ ተጠሪ ወይም ከሌሎች ኃላፊዎች ጋር በመወያየትና ማስታወሻ በመያዝ "ሴቶች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ስላላቸው ሚና" አጠር ያለ ጽሑፍ አዘጋጁና ለክፍሉ በንባብ አሰሙ፡፡

፪. በቡድን በመሆን በተለያዩ ዘመናት በነበሩ ባህላዊ ሥርዓቶች ሴቶች የነበራቸውን ቦታ የሚገልጹ ጽሑፎችን ካነበባችሁ በኋላ ያገኛችሁትን ሃሣብ በማነጻጸር ጽፋችሁ ወይም በንግግር ለክፍሉ አቅርቡ፡፡

፫. ከፍ ሲል በየቡድኑ ከቀረቡት ሃሣቦች ሆነ በማንበብ ካሠባሰባችኋቸው ሀሣቦች በመነሣት የቅስቀሣና ማነቃቂያ ጽሑፍ (በግጥም ይሁን በስድ (ዝርው) አዘጋጁና በቡድን ተጠሪያችሁ አማካይነት ለክፍሉ አቅርቡና ተወያዩበት፡፡

(አስረኛ ክፍል፣ ገጽ 112)

ከቅንጫቢው ውስጥ ዋነኛ ተተኳሪው ሶስተኛው ትዕዛዝ ነው፡፡ በምዕራፍ አራት ላይ የቀረበው የቅስቀሳ ንግግር የትምህርት ልምዱ ማህበረሰብና ጤናን በተመለከተ የሚያጠነጥን ሲሆን በቅንጫቢው ላይ ያለው ደግሞ ሴቶች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ስላላቸው ሚና የሚያትት ነው፡፡ የመጀመሪያው የትምህርት ልምድ ለተማሪዎቹ እንግዳ ሲሆን ሁለተኛ ላይ የቀረበው ግን ቀደም ብለው በተሰጡት ተግባራት በቂ የሆነ መረጃ የሚያገኙበት ስለሆነ ለተማሪዎቹ የሚከብድ የትምህርት ልምድ አይደለም፡፡ ስለሆነም አደረጃጀቱ ከከባድ ወደቀላል እንደሆነ አስረጅዎቹ ያሳያሉ፡፡

መማሪያ መጻሕፍቱ በተናጥል ካላቸው የአደረጃጀት ሥርዓት በተጨማሪ በቅንጅትም ያላቸው ከቀላል ወደ ከባድ አደረጃጀት ሊጤን ይገባዋል፡፡ ከዘጠነኛ ክፍል ላይ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከአስረኛ ክፍል አንጻር ስንመለከታቸው ከቀላል ወደከባድ የተደራጁ ናቸው፡፡ ለዚህም አስረጅ ይሆን ዘንድ ቀጣዮችን ከመጻፍ ተቆርጠው የመጡ ይዘቶች እንመለክት፡፡

**ቅንጫቢ 6፡-** ከዘጠነኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ የሥራ ደብዳቤን በተመለከተ ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

> ፫. የቀረበላችሁን የሥራ ደብዳቤ በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በሚገኙት ክበቦች ውስጥ በአንዱ ሰብሳቢ ሆናችሁ እንደተመረጣችሁ በመገመት የክበቡ አባል ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ለማይገኙ ተማሪዎች የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

(ዘጠነኛ ክፍል፣ 109)

**ቅንጫቢ 7፡-** ከአስረኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ የንግድ ሥራ ደብዳቤን በተመለከተ ተቆርጦ የወጣ ጽሑፍ

> ፬. ቀደም ሲል የቀረበውን የንግድ ሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ መመሪያን እና የንግድ ሥራ ደብዳቤ ናሙና በመከተል በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይና አድራሻ አንድ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ጻፉ፡፡
>
> ፭. ስርዓቱን ጠብቃችሁ መጻፍ አለመጻፋችሁን በአጠገባችሁ ከሚቀመጡ ሌሎች ተማሪዎች ጋር በማስተያየት ተወያዩበት፡፡

(አስረኛ ክፍል፣ 138)

ተቀንጭበው ከወጡ ጽሑፎች መረዳት እንደሚቻለው በዘጠነኛም ሆነ በአስረኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ ላይ የተካተቱ ይዘቶች ደብዳቤን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ላይ የተካተተው ተግባር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተማሪዎቹ እንዲጽፉ የሚያዝ ሲሆን በአስረኛ ክፍል ደግሞ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ተማሪዎቹ በመረጡት ጉዳይ ላይ እንዲጽፉ የሚያዝ ተግባር ተካቷል፡፡ የዘጠነኛ ክፍሉ አጠቃላይ የሥራ ደብዳቤን እንጅ በውስጥ ስላሉ አይነቶች በጥልቀት አልቀረበም ነበር፡፡ በአስረኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ ግን የሥራ ደብዳቤ አይነቶች በሥፋት በማስታዎሻ መልክ የቀረቡ ሲሆን በተግባርነትም የንግድ ሥራ ደብዳቤ እንዲሰሩ ማዘዙ በተመሳሳይ የክብደትና ቅለት መጠን እንዲሁም በተመሳሳይ ቅርጽ አለመቅረባቸውን ያሳያል፡፡ ስለሆነም አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በተመሳሳይ በዘጠነኛ ክፍል በገጽ 11 የቋንቋ ምንነትንና አገልግሎትን የሚመለከት የትምህርት ልምድ ቀርቦ በምክንያትና ውጤት ስልት የቀረበ ጅምር ጽሑፍን ማጠናቀቅን የሚመለከት ተግባር ተካቷል በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ ስለቋንቋ ጥንተ አመጣጥ የሚጠቁሙ የቁሳካላውያንን እና የሀሳባበውያንን መላምት በሚመለከት የተጀመረውን ሀሳብ እንዲቋጩ የሚያዝ ቀርቧል፡፡ ከትምህርት ልምድ አንጻር ተግባራቱን ስናጤን የመጀመሪያው የቋንቋን ምንነትና አገልግሎት ማውሳቱ እንዲሁም የሁለተኛው ጥልቅ የማመዛዘን ችሎታን የሚጠይቀውን የመላምቱን ጥንካሬና ድክመት ማንሳቱ ከመጀመሪያው ይልቅ ጠጠር ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም ከቀላል ወደከባድ እንደተደራጁ ማሳያ ነው፡፡

### 4.2.2 ከተጨባጭ ወደረቂቅ አደረጃጀት

ይህ አደረጃጀት በዋናነት የሚመለከተው የትምህርት ልምዶችን ነው፡፡ ተማሪዎቹ እንዲጽፉባቸው የሚቀርቡ ተጨባጭና ረቂቅ ተብለው መፈረጅ የሚችሉ ጉዳዮች ሲደራጁ ተጨባጩ ቀድሞ መጥቶ ረቂቁ መከተል እንዳለበት በክለሳ ድርሳናት ላይ ተገልጧል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስም የተፈተሸ ይሄው ጉዳይ ነው፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ልምዶች በብዛት ታሪክ ነክ ጉዳዮችና ተጨባጭ ነገሮች ላይ አተኩረው እንዲጽፉ የሚያደርጉ የትምህርት ልምዶች በብዛት ተካተዋል፡፡ በተወሰነ መጠን ረቂቅ ጉዳዮች ቢካተቱም አደረጃጀታቸው ከተጨባጭ ጉዳዮች ጋር ተቀላቅሎ ነው፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ አንድ ላይ ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት ስነቃልን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይቀርቡና ምዕራፍ ሰባት ውስጥ ደግሞ ቆሻሻና አወጋገዱ ቀርቧል፤ በምዕራፍ ስምንት ደግሞ አካል ጉዳተኝነትን፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴንና የመሳሰሉትን የትምህርት ልምዶች በውስጡ ይዟል፡፡ በምዕራፍ አስር ውስጥ ደግሞ እንደገና ክርክርና ሙግት ቀርቧል፡፡ በዚህ አገባብም መጀመሪያ ረቂቅ ጉዳዮች ቀጣይ ተጨባጭ ጉዳዮች ቀርበው እንደገና ደግሞ ረቂቅ ነገሮች ተካተዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል የትምህርት ልምዶች ሙሉ በሙሉ ጠንካራ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የትምህርት ልምዶች ደግሞ በብዛት የተካተቱት ረቂቅ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከተጨባጭ ወደረቂቅ ከማደራጀት አንጻርም ሲታዩ ግን ተመሳሳይ የሆነ ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡ ሁሉም ተጨባጭ የትምህርት ልምዶች ቀድመው መጥተው ረቂቆቹ አልተከተሉም፡፡ አደረጃጀታቸው የተቀላቀለ ነው፡፡ ቋንቋ ነክ የትምህርት ልምዶች መጀመሪያ ተካተው በምዕራፍ ሶስት ደግሞ አካባቢያዊ ገለጻ ያለበት የትምህርት ልምድ ቀርቧል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ማህበረሰብ እና ጤና በትምህርት ልምድነት የተካተተ በመሆኑ የተቀላቀለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉ የመጻፍ ክሂል የትምህርት ልምዶች በዛ ብለው በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ አነስ ማለታቸው የክፍል ደረጃዎች አደረጃጀት ጥሩ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል ላይ አካባቢያዊ ጉዳዮች ሲቀርቡ ተጨባጭ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አተኩረዋል በሌላ በኩል በአስረኛ ክፍል ውስጥ ቀና አመለካከትን የሚመለከትና ረቂቅ ጉዳይ ቀርቧል፡፡ ሌሎችም ጉዳዮች በዘጠነኛ ክፍ ላይ ተጨባጭ የትምህርት ልምዶች እንደበዙና በአስረኛ ክፍል ውስጥ ደግሞ ረቂቅ የትምርት ልምዶች መብዛታቸው ከተጨባጭ ወደረቂቅ እንደተደራጁ ያሳያል፡፡

### 4.2.3 ከቅርብ ወደሩቅ አደረጃጀት

የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች ከተማሪዎቹ ህይወት፣ ልምድ፣ ባህል፣ እድሜና እውቀት ጋር ያላቸው ቅርበት እኩል አለመሆኑን Okunloye (2014) እስዳስረዱ በክለሳ ድርሳናት ላይ ተብራርቷል፡፡ የትምህርት ልምዶቹ ከተማሪዎቹ ህይወት፣ ባህልና ልምድ ጋር ካላቸው ቅርበት አኳያ የሚታይ ሲሆን ይዘቶቹ ደግሞ ከተማሪዎቹ እውቀትና የተነሳውን ይዘት ቀደም ብሎ ከማወቅ አንጻር የሚታይ ነው፡፡ በመጀመሪያ የትምህርት ልምዶች በመጻሕፍቱ ውስጥ ከቅርብ ወደሩቅ ከመደራጀት አንጻር በምን መልኩ እንደተደራጁ ቀርቧል፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል የትምህርት ልምዶች በአመዛኙ ከተማሪዎቹ ህይወትና ባህል ጋር የተቀራረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ያሉትን የትምህርት ልምዶች ለተማሪዎቹ ካላቸው ቅርበት አንጻር ሲታዩ ከተወሰኑ ቦታዎች በስተቀር በአንጻራዊነት ቅርብ የሆኑ የትምህርት ልምደች ቀርበው ራቅ ያሉት ደግሞ

የተከተሉበት አደረጃጀት በመጻሕፍቱ ውስጥ ታይቷል። ቀጣዮቹ ምሳሌዎች ይህንኑ ሀሳብ ያስረዳሉ።

**ቅንጫቢ 8፡-** ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ጭውውት መጻፍ የሚል ተግባር

፫. ቀደም ሲል በክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 2 የከወናችሁትን ጭውውት መሠረት በማድረግ፣ ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባህርያት መካከል አንዱን መርጣችሁ፡-

1. ከ፫-፭ ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ። (በጭውውቱ እንደጭብጡ ሁኔታ ምሣሌያዊና ፈሊጣዊ አባባሎችን መጠቀም ይጠበቅባችኋል።)
2. የጻፋችሁትን ጭውውት አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

**አማራጭ ርዕሶች**

ሀ) አባት፣ እናትና ልጅ

ለ) ርዕሰ መምህር፣ ተማሪና መምህር


ሐ) ሻጭ፣ ገዢና ደላላ

መ) በሽተኛ፣ ሐኪምና አስታማሚ

(ዘጠነኛ ክፍል፣ ገጽ 23)

**ቅንጫቢ 9፡-** ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የጥንቱን ሙግትና የአሁኑን ክርክር የሚገልጽ ተግባር

፫. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ፣ ምንባቡን መሠረት አድርጉና ስዕላዊ መግለጫውን ወደ ጽሑፍ በመቀየር፣ የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የየግልና የጋራ ባህርይ ዘርዝራችሁ በመፃፍ አቅርቡ። እያንዳንዱ ክብም አንዱ በአንዱ ውስጥ ወይም አንዱ ከአንዱ ውጪ ለምን እንደዋለ አስረዱ።



(ዘጠነኛ ክፍል፣ ገጽ 172)

ሁለቱ የትምህርት ልምዶች ለተማሪዎቹ ቅርብ ቢሆኑም የላይኞቹ የትምህርት ልምድ ግን የበለጠ የቀረበ ነው፡፡ በመጀመሪያው ተግባር ላይ ጭውውት እንዲጽፉ በአማራጭነት ከተሰጣቸው ርዕሶች ውስጥ አንዱ "አባት፣ እናት እና ልጅ" ነው፡፡ ይህም በልጅነታቸው ጀምረው የሚያውቁትና ከተማሪዎቹ ህይወት የማይርቅ ነው፡፡ ቀጣዩ አማራጭም ቢሆን "ርዕሰመምህር፣ ተማሪና መምህር" የሚል ሲሆን በትምህርት ህይወት የሚያጋጥም ስለሆነ ቅርብ የትምህርት ልምድ ነው፡፡ ቀሪዎቹም እንዲሁ ከተማሪዎቹ ህይወት የራቁ አይደሉም፡፡

ሁለተኛውን ተግባር ስናይ ደግሞ በጥንቱ ሙግትና በአሁኑ ክርክር ስላለው ልዩነትና አንድነት እንዲጽፉ የሚያዝ ተግባር ነው፡፡ ይህ የትምህርት ልምድ ከላይ ከቀረበው ተግባር አንጻር ሲታይ ሩቅ የሚባል ነው፡፡ ስለሆነም ተግባራቱ የቀረቡበት የትምህርት ልምድ ከቅርብ ወደሩቅ ነው፡፡ በመጽሐፉ በሁለቱ ተግባራት መካከል ያሉ ሌሎች የትምህርት ልምዶችም ደረጃ በደረጃ ከቅርብ ወደሩቅ የተደራጁ ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው ተግባር በፊት (በምዕራፍ አንድ) ያለው የትምህርት ልምድ ግን ከሌሎቹ አንጻር ቅርብ የሚባል አይደለም፡፡ በውስጡ የተነሱ ሀሳቦች ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን ለተማሪዎች እንግዳ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ከሌሎች ቦታዎች ላይም ውስን ችግር ይታያል፡፡ ስለሆነም ከውስን ቦታዎች በስተቀር የዘጠነኛ ክፍል የትምህርት ልምዶች ከቅርብ ወደሩቅ የተደራጁ ናቸው፡፡

ይዘቶቹም ቢሆን ከቅርብ ወደሩቅ የተደራጁ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ላይ በብዛት ተካተው የሚገኙት ከተማሪዎቹ ትምህርታዊ ዳራ ያልራቁና ያላፈነገጡ ሆነው የሚከተሉት ደግሞ ራቅ ያሉት ናቸው፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የመጀመሪያው ይዘት ጅምር ጽሑፍ መጨረስ ሲሆን ይሄ ተግባር ደግሞ በቀደሙት የትምህርት ደረጃዎችም የሚያልፉበት ስለሆነ የሚርቅ አይደለም፡፡ ከዚያም ወደምዕራፉ መጨረሻ አካባቢ የስራ ደብዳቤ መጻፍና የመሳሰሉት ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች ያልተነሱ ጉዳዮች መካተታቸው ከቅርብ ወደሩቅ መደራጀቱን ያሳያል፡፡

በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የትምህርት ልምዶችም ከዘጠነኛ ክፍል በተቀራረበ መልኩ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ብቻ ድክመት ቢታይበትም አደረጃጀቱ ከቅርብ ወደሩቅ የተደራጀ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ ምሳሌ በውሰድ እንመልከት፡፡

**ቅንጫቢ 10፡-** ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የማስታዎሻ አወሳሰድን ከሚመለከት ተግባር ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ

> **ጅ. በምዕራፍ ሦስት ላይ የቀረበውን የማስታወሻ አወሳሰድ ዘዴ በመጠቀም ቀጥሉ የቀረበውን ጽሑፍ ዋናውን መረጃ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡**
>
> ተማሪዎች የቤት ሥራቸውንም ሆነ ጥናታቸውን ሲያከናውኑ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ የሚጠቁሟቸው መምህራንም ሆኑ ሌሎች ደጋፊዎች መኖራቸውን ከተረዱ ትምህርታቸውን በሙሉ ልብ ለመከታተል ይተጋሉ፡፡ ትምህርት በመቀበልም ሆነ በአንዳንድ ግላዊ ችግሮች ምክንያት መሰናክል የሚያጋጥማቸው ተማሪዎች ለትምህ ርታቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመጠቀምም ሆነ በማቅረብ እገዛ የሚገያኙበትን መንገድ ማፈላለግ ቢቻል የበለጠ ውጤት ሊገኝ

(አስረኛ ክፍል፣ 57)

**ቅንጫቢ 11፡-** ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ቀና አመለካከትን የሚመለከት ተግባር

> **ተማሪዎች! ቀጥሉ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጉና ቀና አመለካከት ያላቸውንና የሌላቸውን ሰዎች በማነጻጸር ከሁለት ገጽ ባልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

(አስረኛ ክፍል፣ ገጽ 70)

በመጀመሪያ ላይ የቀረበው የትምህርት ልምድ ስለተማሪዎችና መምህራን የሚገልጽ ስለሆነ በሁለተኛነት ከቀረበው የትምህርት ልምድ ይልቅ የቀረበ ነው፡፡ ለአንድ ሰው ከራሱ በላይ የሚቀርበው ሰው አይኖርም፡፡ በተመሳሳይ ለተማሪዎች ስለሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ከመጻፍ ይልቅ ስለራሳቸው መጻፍ አይቸገሩም፡፡ የማይቸገሩበትም ምክንያት ለተማሪዎቹ ቅርብ ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም በአደረጃጀት መርሁ መሰረት ቀና አመለካከት ስላላቸው ሰዎች ከመጻፋቸው በፊት ስለተማሪዎች ጉዳይ እንዲጽፉ መደረጋቸው ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡ አደረጃጀቱም ከቅርብ ወደሩቅ ነው፡፡

ይዘቶቹም ቢሆኑ ልክ እንደዘጠነኛ ክፍሎች ከሚታወቅ ወደማይታወቅ የተደራጁ ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተካተተው የመጀመሪያው ይዘት የተጀመሩ ጽሑፎችን መቋጨት ሲሆን ሌሎችም በዘጠነኛ ክፍል ላይ የተነሱ ይዘቶች ቀርበው ከዘጠነኛ ክፍል የሌሉ (የማነቃቂያና የቅስቀሳ ጽሑፍ መጻፍ፣ ቃለ ጉባኤ መጻፍና ስዕላዊ መግለጫን ወይም ሰንጠረዥን ወደጽሑፍ መቀየር) ይዘቶችም ቀርበዋል፡፡ ይህም ከቅርብ ወደሩቅ ለመደራጀታቸው አመላካች ነው፡፡

### 4.2.4 ከቀድሞ መጥ አንጻር

ቀድሞ መጥ ከሁለት ጉዳይ አንጻር የሚታይ ነው፡፡ የመጀመሪያው የትምህርቱ ይዘት ቀጥለው ለሚማሩት የትምህርት ይዘት አስፈላጊ ሲሆን ቀድሞ በመምጣት መደራጀት እንዳለበት የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የትምህርት ልምዱም ሆነ ይዘቱ ለልጆቹ ህይወት ከሌሎቹ ጉዳዮች ቀድሞ የሚያስፈልግ ሲሆን የበለጠ የሚያስፈልገው ቀድሞ መምጣት እንዳለበት የሚያደርግ አደረጃጀት እንደሆነ በክለሳ ድርሳናት ላይ በስፋት ተገልጧል፡፡ ስለሆነም ይዘቶቹና የትምህርት ልምዶቹ መደራጀት ያለባቸው ባሉበት የክፍል ደረጃና የዕድሜ ሁኔታ በጣም የሚያስፈልጉት ቀድመው መጥተው ሌሎቹ ደግሞ መከተል እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ በመቀጠል በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች ከአስፈላጊነት አንጻር ምን አይነት የአደረጃጀት ሁኔታ እንደተከተሉ ቀርቧል፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከአስፈላጊነት አንጻር ብዙዎቹ ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡ አንደኛው ይዘት ለሌላኛው መሰረት ሆኖ እያለ ቀድሞ የሚመጣው በጣም የማያስፈልገው እንደሆነ በሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ሥርዓተነጥብን የሚመለከቱ ሁለት ይዘቶች በመመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ እንደተካተቱ በተከታታይነት ሥር ተነስቷል፡፡ በመጀመሪያ (ገጽ 46) የቀረበው ተግባር ከሥርዓተ ነጥብ አይነቶች ውስጥ ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝን የሚመለከት ሲሆን በሁለተኛነት (ገጽ 156) የቀረበው ተግባር ደግሞ አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ቅንፍና ትዕምርተ ጥቅስ ቀርበዋል፡፡፡ ከአስፈላጊነት አንጻር ሲታዩ ግን ቀድሞ መምጣት የነበረበት ተግባር አራት ነጥብ ሆኖ ሳለ የነጠብጣብ ምልክት ቀድሟል፡፡ በየትኛው ጽሑፍ ከዓረፍተነገር ጀምሮ እስከትልቁ ድርሰት ድረስ አራት ነጥብ የግድ የሚያስፈልግ የነጥብ ሥርዓት ነው፡፡ የነጠብጣብ ምልክት ግን

ሁሌም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚወሰነው እንደሚጻፈው ሀሳብ ባህሪና እንደጽሑፉ አይነት ነው፡፡ ምንም አይነት ጽሑፍ ቢኻተት አራት ነጥብ ግን ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከአስፈላጊነት አንጻር ይዘቶቹ በተገቢው መንገድ አልተደራጁም፡፡

በተመሳሳይ ይዘቶች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ይዘቶች መካከል ያለው ተለጣጣቂነትም የተፋለሰ እንደሆነ የሰነድ ምርመራው ውጤት ያሳያል፡፡ ይህንንም ሀሳብ ቀጣዮቹ አስረጅዎች ይበልጥ ያስረዳሉ፡፡

**ቅንጫቢ 12፡-** ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የምዕራፍ ሰባት ተግባራት

**ፊ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቃላቱ በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያሳቸውን አገባባዊ ፍች ጻፉ፡፡ አገባባዊ ፍቻቸውንም ከመዝገበ ቃላት ፍችዎቻቸው ጋር ልዩነት ያለውና የሌለው መሆኑን አነጻጽሩ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** የተዘራው ጤፍ <u>በቅሎ</u> ይታያል፡፡
አገባባዊ ፍች - ቡቃያ ሆኖ፣

1. ጨቤዋ ከነአሮጌ <u>አፎቷ</u> ተሰቀለች፡፡
2. ብርድ፣ ፍርሐትና ድንጋጤ አሰፋን <u>ሰለቁት</u>፡፡
3. በጁ ገፋ ሲያደርገው፣ በሩ ሲከፈት <u>ተንሳጠጠ</u>፡፡
4. በረሃብ የተጠቃ ወገኑን <u>ለመታደግ</u> ቆርጦ ተነሳ፡፡
5. በጎቹን <u>ከጉረኖ</u> አውጥቶ እየነዳ ወደ ገበያ ሔደ፡፡

**ጀ. ባነበባችሁት ጽሑፍ (ቆሻሻና አወጋገዱ) ውስጥ በዋናነት የተነሱ ጉዳዮችን በጽሑፍ አቅርቡ፡፡**

**ፎ. የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ አባባሎች በራሣችሁ አባባል እንደገና ጻፉ፡፡**

1. ማንኛውም የቆሻሻ አይነት እኛንና አካባቢን ሊጐዳ ይችላል፡፡
2. ሁላችንም ብንሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥር…
3. አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጐ ማጨቅና ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት፣
4. በአግባቡ ተጠንቶ ወደተሠራ የቆሻሻ መጣያ ወስዶ መጣል፡፡

(ዘጠነኛ ክፍል፣ ገጽ 124)

ከቅንጫቢው ላይ እንደምናየው ሶስት ይዘቶች በተግባራቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ሁለቱ የአጻጻፍ ሥርዓቶች ሲሆኑ አንደኛው ደግሞ ድርሰት የመጻፍ ተግባር ነው፡፡ የመጀመሪያው ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ሁለተኛው ካነበቡት ምንባብ ውስጥ

ዋናዋና ጉዳዮችን ለይተው በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ የሚያዝ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ ከምንባብ የወጡ ዓረፍተነገሮችን በራሳቸው አባባል እንዲቀይሩ የሚይዝ ነው፡፡ ሶስተኛው ተግባር ለሁለተኛው ተግባር አስፈላጊ ስለሆነ ቀድሞ መምጣት ነበረበት፡፡ አንድን ምንባብ አንብቦ ዋና ዋናውን ሀሳብ በመለየት በጽሑፍ ለማስፈር የሌሎችን ሀሳቦች በራስ አባባል የመቀየር ችሎታ ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን በቀረቡት ተግባራት ውስጥ ያለው አደረጃጀት ይህን ግንዛቤ ውስጥ አላስገባም፡፡ ስለሆነም በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የመጻፍ ክሂል የተለያዩ ተግባራት ሲደራጁም ከአስፈላጊነት አንጻር ድክመት እንዳለባቸው የሚያሳይ አስረጅ ነው፡፡

አንዳንድ ቦታዎች ላይ ግን ከአስፈላጊነት አንጻር ጥሩ የሆነ አደረጃጀት የታየባቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፉ ውስጥ የሥራ ደብዳቤ መጻፍ የሚልና አስተዋጽዖ መንደፍ የሚሉ የተለያዩ ተግባራት የተካተቱ ሲሆን ቀድሞ የመጣው አስተዋጽዖ መንደፍ ነው፡፡ ይህም ከአስፈላጊነት አንጻር ሲታይ ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ለተማሪዎቹ ከሥራ ደብዳቤ መጻፍ ይልቅ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው አተዋጽዖ መንደፍ ነው፡፡ የትኛውንም አይነት ጽሑፍ በሚጽፉበት ወቅት አስተዋጽዖ መንደፍ ከቻሉ ስለማይቸገሩ ቀድሞ መካተቱ በተወሰነ መልኩ ጠንካራ ጎን እንዳለው ማሳያ ነው፡፡

የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ተግባራት ደግሞ ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጻፍ ውስጥ ከተካተቱ ተግባራት በተሻለ ከአስፈላጊነት አንጻር ጥሩ የሆነ አደረጃጀት አላቸው፡፡ ለወደፊቱ ተግባር በጣም አስፈላጊ የሚባሉ ይዘቶች በአብዛኛው ቀደም ብለው የመጡ ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ አስረጅዎች ቀርበዋል፡፡

**ቅንጫቢ 13፡-** ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የምዕራፍ አስር ተግባራት ተቆርጠው የወጡ

**፭. ከዚህ በታች የሚቀርቡላችሁን አያያዥ ቃላት በመጠቀም "ሥራና ምርትን በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ስለዚህ | ይሁን እንጂ | ነገር ግን |
| በመሆኑም | ወይም | ለምሳሌ |
| እና | ባንጻሩ | ደግሞ |

**፮. በሠንጠረዥ የቀረበላችሁን መረጃ መሠረት በማድረግ ርዕስ ሰጥታችሁ፣ አንድ አጭር ጽሑፍ ጻፉ፡፡**

**፫. ቀጥሎ በጽሑፍ የቀረበላችሁን ምንባብ በሚገባ በማንበብ ከጽሑፉ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጉዳዮችን በመለየት አስቀምጡ።**

(አስረኛ ክፍል፣ ገጽ 134-135)

ተቀንጭበው የወጡ ተግባራት በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የአጻጻፍ ሥርዓትን የሚመለከቱ ናቸው። በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱ ተግባራት ቅደም ተከተል ሲታይ አስፈላጊነትን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው። ተማሪዎቹ የተለያዩ ጽሑፎችን በደንብ ለመጻፍ አያያዦችን በደንብ ሊያውቁና ሊጠቀሙባቸው ይገባል። ከዚያ በሰንጠረዥ የቀረበን መረጃ በተሳካ መንገድ ሊጽፉት ይችላሉ ጽሑፎችንም በሰንጠረዥ ሊያደራጁ ይችላሉ። ስለሆነም በጣም አስፈላጊ የሆነው ተግባር ቀድሞ መጥቷል፤ ሌሎችም ተከትለዋል።

አንድ ተጨማሪ አስረጅ እንመልከት። በመጽሐፉ ምዕራፍ አራት ላይ በመጀመሪያ እውነታንንና የግል አስተያየትን እንዲለዩ የሚያዝ ተግባር ቀርቦ በመቀጠል ደግሞ የቃለጉባዔ አጻጻፍ ተካቷል። ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ ቃለጉባኤን ከመጻፋቸው በፊት እውነታ የሆኑ ጉዳዮችንና የግል አስተያየቶችን ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ አደረጃጀቱም ከአስፈላጊነት አንጻር ጥሩ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

የየክፍል ደረጃዎችን አደረጃጀት በተመለከተ ከአስፈላጊነት አንጻር ሲታዩ ጠንካራ ጎናቸው ጎልቶ ይታያል። አስፈላጊ የሚባሉ ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶች በዘጠነኛ ክፍል ላይ በስፋት የተካተቱ ሲሆን በዘጠነኛ የተካተቱ ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶችን መሰረት አድርገው ደግሞ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ቀርበዋል። ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት የሚል የትምህርት ልምድ የቀረበ ሲሆን በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ የቋንቋ ጥንተ አመጣጥና ባህርያት ተካተዋል። ስለቋንቋ ጥንተአመጣጥና ባህሪያት ከመነሳቱ በፊት ምንነቱን ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በዘጠነኛ ክፍል ምንነት ቀድሞ በመቅረብ በአስረኛ ክፍል ላይ ደግሞ ጥንተአመጣጡና ባህሪያቱ መካተታቸው ጥንካሬውን የሚያሳይ ነው።

ከይዘት አንጻርም አስፈላጊነትን ታሳቢ ያደረገ አደረጃጀት የተከተለ ነው። ለዚህ ማሳያ አንቀጽን በተመለከተ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን

ይዘተቶች እንመልከት፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ገጽ 45 የአንቀጽ ምንነትንና ባህሪያት የቀረቡ ሲሆን በአስረኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ገጽ 39 የአንቀጽ ቅርጾች የሚል ይዘት ተካቷል፡፡ ስለአንቀጽ ቅርጽ ከመወራቱና ተግባርም ከመሰጠቱ በፊት ስለአንቀጽ ምንነትና ባህሪያት ቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ "አንቀጽ ኀይለቃልና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ይይዛል፡፡" የሚለውን እሳቤ ያላወቀ ተማሪ የአንቀጽ ቅርጽ ሊገባው አይችልም፡፡ ይህም ከአስፈላጊነት አኳያ ጥሩ አደረጃጀት እንዳለው ማሳያ ነው፡፡

የማስታዎሻዎቹና የተግባራቱ አደረጃጀት ከአስፈላጊነት አደረጃጀት አንጻር ድክመት ታይቶበታል፡፡ በአብዛኛዎቹ የዘጠነኛ ክፍል እና ጥቂቶቹ የአስረኛ ክፍል ይዘቶች ሲታዩ ተግባራት ይቀድሙና ማስታዎሻዎቹ ይከተላሉ፡፡ ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍ* ገጽ 46 ላይ ስርዓተ ነጥብን የሚመለከት ተግባር ቀርቦ ስለሥርዓተ ነጥብ የቀረበው ማስታዎሻ ይከተላል፡፡ በአስረኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍም* ሌላ ምሳሌ እንጥቀስ፡፡ በገጽ 54 ላይ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር የተሰኘ ተግባር ቀድሞ ይቀርብና መስታዎሻው ይከተላል፡፡ ተግባራቱን በሥርዓት ለማከናወን ማስታዎሻዎቹ ቀድመው መምጣት ይኖርባቸው ነበር፡፡ ተግባራቱን ከሰሩ በኋላ ማስታዎሻዎቹ መቅረባቸው አስፈላጊነታቸውን ይቀንሰዋል፡፡

## 4.3 ከውህደት አንጻር

ውህደት የአንድ ትምህርት ይዘት ከሌሎች ትምህርት ይዘቶች ጋር ተዋህዶ መቅረብ መሆኑን በክለሳ ድርሳናት ላይ አውስተናል፡፡ ስለሆነም የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከሌሎች ትምህርት ይዘቶች ጋር ተደራጅተው የቀረቡበት መንገድ በዚህ ንዑስ ርዕስ ቀርቧል፡፡

ከዚህ ቀደም በተከታይነት ሥር በትምህርት ልምድነት የቀረቡ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች፣ ሥነጽሑፋዊ ጉዳዮች፣ አካባቢያዊ ጉዳዮች፣ መገናኛ ብዙኀን፣ ባህላዊ ጉዳዮች፣ ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ አመለካከትን የሚመለከቱ ጉዳዮችና ሥራን የሚመለከቱ ጉዳዮች እንደሆኑ ተገልጧል፡፡ ይህም ቋንቋ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የጎን ለጎን ግንኙነት እንዲኖረው ተደርጎ እንደቀረበ ያሳያል፡፡ በትምህርት ልምድነት ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ብቻ አልቀረቡም፡፡ በተጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ ታሪክ፣ ጤና፣ ስፖርት፣ ባህልና የመሳሰሉት አብረው ተካተዋል፡፡ ቀጣዮቹ አስረጅዎችን ይህንን እውነታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ገጽ 24 ላይ አንቀጽ ለመጻፍ በትምህርት ልምድነት የቀረበው ባህላዊ ምግቦች የሚል ነው፡፡ በገጽ 46 ሥርዓተ ነጥብን ለማለማመድ በቀረበው ተግባር ጤና ነክ የትምህርት ልምድ ተካቷል፡፡ በሌላ በኩል በገጽ 137 አያያዥን ለማስተማር የቀረበው የትምህርት ልምድ ታሪክ ነው፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ውህደቱን ታሳቢ ያደረገ አደረጃጀትን መከተላቸውን ለማሳየት የቀረቡ አስረጅዎች ናቸው፡፡

በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም አሳጥሮ ለመጻፍ የቀረበው የትምህርት ልምድ አካባቢያዊ ገጽታ (መልክዓምድራዊ ገለጻ) ነው፡፡ በገጽ 57 ከጽሑፍ ማስታዎሻ በመውሰድ ጽሁፍ ለመጻፍ በትምህርት ልምድነት የቀረበው ጤና ነክ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በገጽ 112 ደግሞ ማስታዎሻ በመያዝ ጽሑፍ ለመጻፍ የቀረበው ጉዳይ የትምህርት ልምድ ነው፡፡ ይህም ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ከሌሎች ትምህርት ይዘቶች ጋር ተዋህዶ መቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም የሁለቱም መጻሕፍት ከውህደት አንጻር ሲታዩ የተሳካ አደረጃጀት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዐብይ ዓላማ በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች የተደራጁበትን መንገድ መፈተሸ የሚል ሲሆን በአደረጃጀቱም በሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት አንጻር ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው ተፈትሸዋል፡፡

ጥናቱን ለማጥናት እገዛ የሚያደርጉ የይዘቶችና የትምህርት ልምዶች አደረጃጀትን የሚመለከቱ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችና ጽንሰሀሳባዊ ጉዳዮች በክለሳ ድርሳናት ስር ተዳሰዋል፡፡ ንድፈ ሀሳቦች ከጥናቱ ዓላማ ጋር የተገናኙና በምዕራፍ አራት ላይ ለትንተና የሚያግዙ ናቸው፡፡ ጥናቱ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ስላሉ ተተኳሪ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ዙሪያ ላይ ትኩረቱን በማድረጉ የመረጃ ምንጮቹ መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ስለሆነም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰበው መረጃም በአይነታዊና በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትኗል፡፡ የትንታኔው ውጤትም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

- በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከተወሰኑት በስተቀር በበቂ የድግግሞሽ መጠን እንዳልቀረቡ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ያሉ ይዘቶችም በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ በበቂ መጠን ተደጋግመው አልቀረቡም፡፡ ስለሆነም የይዘቶች ተከታታይነት ድክመት እንዳለበት ታይቷል፡፡

- በዘጠነኛም ሆነ በአስረኛ ክፍል ያሉ የትምህርት ልምዶች የድግግሞሽ መጠን ግን ከይዘቶች በተሻለ ጥሩ የድግግሞሽ መጠን አላቸው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ያሉት የትምህርት ልምዶች በአስረኛ ክፍል ተደግመው ከመምጣት አንጻር ግን ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ልምዶቹ በተናጥል መማሪያ መጻሕፍቱ

ውስጥ ያሉት ከትምህርት ልምዶች ተከታታይነት አንጻር ጠንካራ ጎን ሲኖራቸው የሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት ቅንጅታዊ አደረጃጀት ግን ድክመት ታይቶበታል፡፡

- በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የመጻፍ ክሂልና የትምህርት ልምዶች በየደረጃው በከፊል ከቀላል ወደከባድ የተደራጁ ሲሆኑ በከፊል ደግሞ ከከባድ ወደቀላል ተደራጅተዋል፡፡ የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ግን ከዘጠነኛ ክፍል በተሻለ መልኩ በርካታ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ እንደተደራጁ የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡ የአስረኛ ክፍሉ ከጥቂት ተግባራት በስተቀር ከቀላል ወደከባድ እንደተደራጁ የሰነድ ፍተሻው መረጃ ያሳያል፡፡ ሁለቱ መማሪያ መጻሕፍት በቅንጅት ከቀላል ወደ ከባድ አደረጃጀት አንጻር በትክክል እንደተደራጁ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ማለትም በአስረኛ ክፍል የተካቱት የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች ያላቸው አደረጃጀት ከቀላል ወደከባድ ነው፡፡

- በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ልምዶች ከተጨባጭ ወደረቂቅ አደረጃጀት አንጻር ሲታዩ ያላቸው የክፍል ደረጃ ተናጥላዊ ባህሪ በትክክል ከተጨባጭ ወደረቂ ያልተደራጁ ሲሆን ሁለቱ መጻሕፍት በቅንጅት ሲታዩ ግን  የአደረጃጀት መርሁ በሚያዘው መልኩ እንደተደራጁ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

- በሁለቱም የክፍል የቀረቡ የትምህርት ልምዶች በአመዛኙ ከተማሪዎች ህይወት ጋር ቅርበት ያላቸው ሲሆኑ ያሉት የትምህርት ልምዶችም ከቅርብ ወደሩቅ ከመደራጀት አንጻር ውስን ድክመቶች ቢታዩባቸውም አብዛኛዎቹ ግን ከቅርብ ወደሩቅ የተደራጁ ናቸው፡፡

- በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ከአስፈላጊነት የአደረጃጀት መርህ አንጻር ሲታዩ ድክመታቸው ጎልቶ የታየ ሲሆን በአስረኛ ክፍል ውስጥ የታዩት ግን አብዛኛዎቹ ይዘቶች ሲደራጁ በጣም አስፈላጊ የሆኑት ቀድመው እንደተደራጁ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ከዚህ አደረጃጀት አንጻር ያላቸው ጥምረታዊ አደረጃጀት ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ለአስረኛ ክፍል የመጻፍ ክሂል ይዘት አስፈላጊ የሆኑ ይዘቶች በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፡፡ የማስታዎሻዎቹና

የተግባራቱ አደረጃጀት ግን በአብዛኛው የተደራጁት ተግባራቱ ቀድመው ማስታዎሻዎቹ ደግሞ ተከትለው ነው፡፡ ይህም ተግባራቱ እንዴት እንደሚተገበሩ መመሪያዎችና አስረጅዎች ሳይቀርቡላቸው ቀጥታ ወደተግባራቱ እንዲያመሩና ለመስራትም እንደሚቸገሩ የሚጠቁም ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጉዳይ አንጻር ድክመት እንዳለበት የግምገማው ውጤት አሳይቷል፡፡

- በሁለቱም መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅና ከአስፈላጊነት አንጻር ከመደራጀት አንጻር በከፊል ጥሩ አደረጃጀት ሲኖራቸው በከፊል ደግሞ ድክመት ታይቶባቸዋል፡፡ ከቅርብ ወደሩቅ ያላቸው አደረጃጀት ግን ጠንካራ ጎኑ ያመዝናል፡፡ በመሆኑም የይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ተለጣጣቂነት በአብዛኛው ድክመቱ እንደሚያመዝን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡

- የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ተዋህደው ከመቅረብ አንጻር ሲታዩ በዘጠነኛም ሆነ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ተግባራት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ተዋህደው የቀረቡ እንደሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

በጥናቱ ግኝት የመጻፍ ክሂል ይዘቶችንና የትምህርት ልምዶች አደረጃጀትን በሚመለከት ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎኖች ታይተዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስም በተገኙ ደካማ ጎኖች መነሻነት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚመረጡ ይዘቶችም ሆኑ የትምህርት ልምዶች ሲደራጁ ተማሪዎቹ የታቀደለትን ግብ እንዲመቱ ተደጋግመው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በጥናቱ ግኝትም የተግባራቱ የድግግሞሽ መጠን አናሳ እንደሆነ ስለተረጋገጠ መማሪያ መጻሕፍትን የሚያሻሽሉም ሆኑ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ልዩ ትኩረት ተግባራቱን በበቂ የድግግሞሽ መጠን ቢያደራጇቸው የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል አስፈላጊ ነው፡፡

- ተማሪዎቹ ተስፋ ቆርጠው ለመጻፍ ክሂል አሉታዊ አመለካከት እንዳይኖራቸውና ደረጃ በደረጃ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የቀረቡ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶችን ከቀላል ወደከባድ ማደራጀት ተገቢ ነው፡፡ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች በሚያዘጋጇቸው መጻሕፍት መምህራንም በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ይህን አደረጃጀት ቢተገብሩ የተሻለ ነው፡፡

- ተማሪዎች ትምህርቱ ይበልጥ የሚገባቸው ከረቂቅ ጉዳዮች ይልቅ ተጨባጭ ጉዳዮች ቀድመው ሲቀርቡላቸው በመሆኑ በመማሪያ መጻሕፍቱም ይህ ተግባራዊ ቢደረግና ለህይወታቸው ቅርብ የሆኑ የትምህርት ልምዶች ቀደም ብለው ቢቀርቡላቸው ለትምህርቱ ስኬታማነት ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡

- በጥናቱ ግኝት ሁሉም ይዘቶች ከአስፈላጊነት አንጻር እንዳልተደራጁ ተጠቁሟል፡፡ መምህራንም ክሂሉን ሲያስተምሩ አስፈላጊ ይዘቶችን በማስቀደም ቢያስተምሩ መማሪያ መጻሕፍቱም በዚሁ መልኩ ቢዘጋጁ ጥሩ ውጤት ይገኛል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ማረው ዓለሙ፡፡ (1996)፡፡ *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ሥነ-ጥበብና ትምህርት ሚኒስተር፡፡ (1954)፡፡ "የአንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት"፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በሥነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋሰው፡፡* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ተስፋየ ሸዋየ፡፡ (1981)፡፡ "ስነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር"፡፡ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋየ ሸዋየ፡፡ (1986)፡፡ *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር፡፡* አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ተሻለ ክፍሌ፡፡ (2005)፡፡ "በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት"፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፡፡ (2004)፡፡ *የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ፡፡* ዱባይ፤ አልጉሬር አታሚ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፡፡ (2004)፡፡ *የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ፡፡* ዱባይ፤ አልጉሬር አታሚ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፡፡ (2004)፡፡ *የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ፡፡* ዱባይ፤ አልጉሬር አታሚ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት፡፡ (1982)፡፡ *ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አታሚ ድርጅት፡፡

አስቴር ሳሙኤል፡፡ (1998)፡፡ “የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ (በሆሳዕና ከተማ)”፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አስቻለው ቦጋለ፡፡ (2000)፡፡ “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጽህፈት ክሂል ትምህርት የአቀራረብና የማስተማር ዘዴዎች ፍተሻ”፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ኢትዮጵያ ተክሌ፡፡ (2009)፡፡ “በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋሉት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (ከ5ኛ-8ኛክፍል) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል?”፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ጽጌ ታፈሰ፡፡ (1992)፡፡ “ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል? በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛ እርከን (5-8) በተዘጋጁት የአማርኛ መጻህፍት ላይ የተደረገ የይዘት ትንተናና ግምገማ”፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ (1996)፡፡ *ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2002)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡* ባህር ዳር፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Arias, I.J. (2007). Selecting Reading Materials Wisely. Retrieved January 12, 2018. From፡ www.http://revistas.una.ac.cr/index.php/letras/article/viewFile/%20648/583

Condon, W. and Butler, W. (1997). *Writing The Information Super High Way*. Boston: Avia com company.

Creswell, J. W. (2012). *Planning, Conducting and Evaluating Quantitative and Qualitative Research*. USA; Pearson Education, Inc.

Creswell, J. W. (2009). *Research Design*. United States of America: SAGE Publications, Inc.

Cunningsworth, A. (1995). *Choosing Your Course Book*. Oxford: Heinemann.

General Practice Supervisors Australia. (2014). Vertical And Horizontal Learning Integration In General Practice. Retrieved January 10, 2018. From: http//www.gpsupervisorsaustralia.org.au/wp-content/uploads

Harmer, J. (1991). *The Principle of English Language Teaching*. London: Longman Group UK Limited.

Janet, E. (2003). Writing as a Model of Learning: *TESOL QURTY*. Vol 37, No. 21, PP. 345-351.

Kenneth, O. (1997). *Developmental Psychology.* Univeresity of Mississipi: HBI Publisher.

Nacira, G. (2010). "Identification and Analysis of Some Factors Behind Students' Poor Writing Producctions The Case Study of 3rd Year Students at The English Department-Batna Universisty". Dissertation Submitted in Partial Fulfillment for the Requirements PhD. (Unpublished).

NTU. (2017). Origions and Evolution of Writing System. Retrieved April 12 2018. From: http://blogs.ntu.edu.sg-wiki-chapter-17

Nunan, D. (1988). *Syllabus Design*. Oxford: Oxford University Press.

Nunan, D. (1992). *Research Methods in Language Learning*. Cambridge: Cambridge University press.

Nunan, D. (2000). *Language teaching methodology: Textbook for teachers*. Malaysia: Longman.

O'Farrell, R. (2018). The Importance of Good Writing skills in the Workplace. Retrieved January 18, 2016. From: https://www.google.com.et/url?sa

Okunloye, R. W. (2014). *Curriculum Innovetion and Change: Fundamental of Curriculum Development.* Nigeria: BAMITEX Printing and PUB.ENT.

Prince Edward Island. (2008). Evaluation and Selection of Learning Resources. Retrieved January 7, 2018. From http://www.gov.pe.ca/educ

Raimes, A. (1983). *Techniques in Teaching Writing*. Oxford: Oxford University Press Inc.

Reid, J. M. (1993). *Teaching ESL writing*. Englewood Cliffs, N.J.; Printice Hall Regents.

Richard P. K., Underhile, R. and Andrew F. W. (2007). Horizontal and Vertical Structures: *The Dynamics of Organization in Higher Education.* Vol. 93, No. 4.

Richards, J.C. (1990). *The Language Teaching Matrix*. Cambridge: Cambridge University Press.

Steve, K. (2009). Dimension And Principles of Curriculum: Design Module Ⅱ. Retrieved January 7, 2018. From: http://www.slideshare.net/pyrochem100/curriculum-dimensions

Taba, H. (1962). *Curriculum Development Theory and Practice*. New York: Harcourt Brace Jovanovich Inc.

Tyler, R.W. (1949). *Basic Principles of Curriculum and Instruction*. Chicago: The University of Chicago Press.

Ur, P. (2006). *A Course in Language Teaching: practice and theory.* (13th edition). Cambridge: Cambridge University Press.

Widdowson, H.G. (1978). *Teaching Language of Communication*. Oxford: Oxford University Press.

WordPress.com. (2016). The Meaning of Curriculum Content And Learning Experience. Retrieved January 8 2018. From: https://hyattractions.wordpress.com/2016/12/07/the-meaning-of-curriculum-content-and-learning-experiences/

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው "የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ትንተና (በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና በውስጥ የተጠቀምኳቸው የተለያዩ ጽሑፎች ምንጫቸውን የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________________

ፊርማ ____________________________

ቀን______________________________

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ አዲስ አበባ